# በማጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጬች ትንተና

(በጋምቤላ ክልል በመጃንግ ዞን በሚገኘው የሰሙይ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በ

ይማም አህመድ

ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጅማ ዮኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ

ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ

አማርኛ ትምህርት ክፍል

ነሐሴ 2016 ዓ ም

ጅማ ኢትዮጵያ

# በማጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ድርሰትሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና

(በጋምቤላ ክልል በመጃንግ ዞን በሚገኘው የሰሙይ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በ

ይማም አህመድ

አማካሪ

ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጅማ ዮኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ

ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ

አማርኛ ትምህርት ክፍል

ነሐሴ 2016ዓም

ጅማ ኢትዮጵያ

## ማረጋገጫ

"በማጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና" በሚል ርዕስ በጋምቤላ ክልል በማጃንግ ዞን በሚገኙ የሰሙይ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒትስ ኮሌጅ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበው ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑን እና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም ዋቢ የተደረጉ ናቸው። የጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም---------------------------------ፊርማ------------------ቀን-------------

የአማካሪ ስም-------------------------ፊርማ----------------ቀን-----------

የፈታኝ ስም-----------------------------ፊርማ----------------ቀን--------

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ

ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ

አማርኛ ትምህርት ክፍል

በማጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ድርሰትሲጽፉ የሚፈጽሟቸው

ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና

(በጋምቤላ ክልል በመጃንግ ዞን በሚገኘው የሰሙይ ትምህርት ቤት 7ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በይማም አህመድ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ----------------------ፊርማ -----------ቀን--------------

የውስጥ ፈታኝ ------------------------- ፊርማ ------------- ቀን----------

የውጭ ፈታኝ --------------------------- ፊርማ -------------ቀን ------

## ምስጋና

በመጀመሪያ ከብዙ ፈተናዎች በኋላ ለዚህ ያበቃኝን ፈጣሪየን አመሰግነዋለሁ፡፡ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ከትልመ ጥናቱ ጀምሮ ስህተቶችን በማረም ያገዙኝንና ያበረታቱኝን አማካሪየን ዶክተር ምህረት ሳዳሞን እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በተጨማሪም ለዶክተር ለማ ንጋቱ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል በሃሳብ ድጋፍ ያደረገችልኝን ውድ ባለቤቴን ዘሃብ አሰፋን ሳላመሰግን አላልፍም፡፡ ከጎኔ ሆነው አይዞህ ያሉኝን ውድ እህቴን ሶፍያ አህመድን ፣ ወንድሜን ፈንታው አህመድን እንዲሁም ባለቤቱን ከድጃ በድሩን አመሰግናችዋለሁ፡፡ እንዲሁም በኮምፒዉተር ጽህፈትና አስተያየት በመስጠት የረዳኝን መምህር ሙክታር አስማማዉና ባለቤቱ ከሚላ አሰፋን ምስጋና ይድረሳችሁ እላለሁ፡፡ በመጨረሻም ለሰሙይ ትምህርት ቤት መምህራንና ተማሪዎች መረጃ ስለሰጡኝ ታላቅ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ፡፡

## አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጋምቤላ ክልል በማጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ በሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማጃንግ ቋንቋ አፍቻዉን የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች፣ የስህተት ምንጮችና የድግግሞሽ መጠን መለየት ነው ። ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስም አጥኝው የተጠቀመዉ የስህተት ምንጮችን ለመለየት አይነታዊ ምርምር ዘዴን የስህተት መጠንና ድግግሞሽን ለመለየት ደግሞ መጠናዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል። የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ በአመቻ ናሙና አመራረጥ ተመርጠዋል። ይህም የአጥኚውን የገንዘብ አቅምና የመረጃ ክፍተት ለመሙላት ምቹ በመሆኑ ነው ። የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ አላማ ተኮር ነው ይህም የሆነዉ አፋቻዉን በማጃንግ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች አንቀጽ ለመጻፍ የሚደርሱበት ክፍል በመሆኑ ነው ። ይህም የጽሁፍ ስህተቶችን ገና በ እንጭጩ ለማስወገድ የሚቻልበት የክፍል ደረጃ በመሆኑ ነው። የመምህራን ናሙና አመራረጥ ደግሞ በትምህርት ቤቱ ሁለት አማርኛ መምህራን ብቻ በመሆናቸው በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ በትምህርት ቤቱ በማጃንግ ቋንቋ አፋቻዉን የፈቱ 20 ወንዶችና 30 ሴቶች በድምሩ 50 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በጠቅላይ ናሙና ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በተማሪዎቹ በተመረጡ ድርሰቶች ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅተው ለተማሪዎች በማቅረብ ጥናቱ ተካሂዷል ። እንዲሁም ለመምህራን የቃለ መጠይቅ በማድረግ የተፈለገዉን መረጃ በመሰብሰብ ለጥናቱ አስፈላጊዉን ግብአት አበርክተዋል ። በመሆኑም አጥኚዉ የሰበሰበዉን መረጃ በአግባቡና በጥንቃቄ በማዋቀር በአይነታዊና በመጠናዊ የምርምር ዘዴ ተንትኖ ለአንባቢ አቅርቧቸዋል ። በጥናት ውጤቱ መሰረትም የተተኳሪ ተማሪዎቹ የስህተት ምንጮች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የዉስጥ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አመራረጥና የማስተማር ዘዴዎች ድክመት፣ የማህበራዊና ስነልቦናዊ ጉዳዮች የሚሉት ነጥቦች ዋናዋናዎቹ እንደሆኑ ተረጋግጧል። በመጨረሻም አጥኚዉ ለችግሮቹ መፍትሄ ማፈላለግ ላይ የሚመለከታቸዉ አካላት ሁሉ የበኩላቸዉን ድርሻ እንዲወጡ አደራ በማለትና የግል አስተያየቱን በመስጠት ጥናቱን አጠናቋዋል።*

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

1. ምስጋና ....... i
2. አጠቃሎ ....... ii

**3.** ....... ii

ማውጫ ....... iii

1.1. የጥናቱ ዳራ ....... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....... 3

1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ....... 4

1.4. የጥናቱ ዋና አላማ ....... 4

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ....... 5

1.6. የጥናቱ ወሰን ....... 5

ምዕራፍ ሁለት ፡ ክለሳ ድርሳናት ....... 6

2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝቶች ....... 7

2.1.1 የጽህፈት ክሂል ምንነት ....... 7

2.1.2 የመጻፍ ክሂል አላማ ....... 8

2.1.3 የጽህፈት ክሂል ጠቀሜታ ....... 8

2.1.4 የጽህፈት ክሂል ማስተማር ....... 9

1. 2.2 የስህተት ምንነት ....... 10

2.2.1 የስህተት ትንተና አስፈላጊነት ....... 12

2.3.1 የጽህፈት እርማት አይነቶች ....... 13

1.6.1. 2ሁሉንም ስህተቶች ማረም ....... 13

1.6.2. የተመረጡ ስህተቶችን ብቻ ማረም ....... 14

1.6.3. ተማሪው ስህተቱን ያርም ዘንድ ጥቆማ መስጠት ....... 14

1.6.4. ተማሪዎችን ለይቶ በማስወጣት ስህተታቸውን እንዲያርሙ ማደረግ ....... 14

2. 2.4 የስህተት ምንጮች ....... 15

2.4.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ....... 16

2.4.2 የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ........ 17
2.4.3. የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማር ዘደዎች ድክመት ........ 18
ምዕራፍ ሶስት ፡የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ........ 32
3.1 የጥናቱ ዘዴ........ 32
ምዕራፍ አራት ........ 37
የመረጃ ትንተና እና ማብራሪያ........ 37
4.1 የመረጃ ትንተና........ 37
**4.1.2. በድርሰቶች ውስጥ የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች** ........ 39
4.2 ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 51
**ምዕራፍ አምስት** ........ 63
**ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ** ........ 63
ዋቢ ጽሁፎች........ 66
አባሪዎች........ 73

የሰንጠረዥ ዝርዝር

ሰንጠረዥ 1 የድርሰት ስህተቶችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 38

ሰንጠረዥ 2በድርሰቶች ውስጥ የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች (ድርሰት አንድ)........ 39

ሰንጠረዥ 3 ፡ በድርሰቶች ውስጥ የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች (ድርሰት ሁለት) ........ 40

ሰንጠረዥ 4 3፡ በድርሰቶች ውስጥ የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች (ድርሰት ሁለት)........ 42

ሰንጠረዥ 5 በድርሰት ሁለት የሆህያትን አጻጻፍ ስህተት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 43

ሰንጠረዥ 6 የስርዓተ ነጥብ ስህተትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 45

ሰንጠረዥ 7 የስርዓተ ነጥብ ስህተትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 46

ሰንጠረዥ8 በድርሰት አንድ ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ስህተትን የሚያሳይ ........ 48

ሰንጠረዥ9 ድርሰት ሁለት ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ስህተትን የሚያሳይ ........ 48

ሰንጠረዥ 10 የአማርኛ መምህራን ድርሰት የማጻፍ ሁኔታን የሚያሳይ ትንታኔ........ 51

ሰንጠረዥ 11 11 የድርሰት ጽሁፍ የቤት ስራ መስጠትን የሚያሳይ ትንታኔ ........ 52

ሰንጠረዥ12 መምህራን የድርሰት ጽሁፍ የቤት ስራን የመከታተል ሁኔታን የሚያሳይ ትንታኔ ........ 53

ሰንጠረዥ 13 13 በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት የመጻፍ ፍልጎትን በተመለከተ የሚያሳይ ትንታኔ........ 54

ሰንጠረዥ 14 በተማሪው መጽሃፍ ውስጥ ያለውን መልመጃ መስራትን በተመለከተ የሚያሳይ ትንታኔ.. 54

ሰንጠረዥ15 የአማርኛ መምህሩ ከተማሪው መጽሃፍ ውጭ ማስተማር አለማስተማሩን የሚያሳይ ትንታኔ ........ 55

ሰንጠረዥ16 በአማርኛ ድርሰት መጻፍ የመፍራት እና ያለመፍራት ጉዳይ በተመለከተ የሚያሳይ ትንታኔ 56

ሰንጠረዥ 17 መረጃ የሰጡ መምህራንን የሚያሳይ ትንታኔ........ 58

## ምዕራፍ አንድ ፡ መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ አላማው የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የመጻፍ እና የማንበብ ክሂሎችን ማዳበር ነው።ይህንን አላማም ዳር ለማድረስ ተገቢውን ትኩረት የሰጠ የትምህርት ይዘት አዘጋጅቶ ማቅረብ ያስፈልጋል ።

ጽህፈት እንደ ማዳመጥ እና መናገር ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ኣይደለም። በመሆኑም አፍ ፈት ሆነ ኢ-አፍ ፈት ቋንቋ ተናጋሪወች በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ልምምድ እና ትምህርት ብቻ የሚዳብር ነው። ስለሆነም በአንድ የተማሪ የመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የሚቀርብ የትምህርት ይዘት ለአንድ ክሂል የማያዳላ እና ሁሉንም በተገቢው መንገድ አጣጥሞ የያዘ መሆን ይኖርበታል በማለት Harmer (1991 : 50) ይገልጻሉ። የጽህፈትን ምንነት አስመልክቶ Lado(1964:43) " ጽህፈት በሚታዩ እና ልንረዳቸው በምንችላቸው ምልክቶች ንግግርን መወከል ነው"። እነዚህንም ምልክቶች ቋንቋውን የሚያውቁ ሰወች ሊያንቧቸው እና ውክልናቸውንም ሊረዷቸው ይገባል በማለት ገልጸዋል።

Celce (1991:105) ደግሞ "ጽህፈት በአንድ የተማረ ማህበረሰብ ዉስጥ በግንባር የሚጠቀስ ባህልን፣ ታሪክን፣ሚስጥርን እና ወዘተ በማስረጃነት ለማስቀመጥ የተቀመጠውንም ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችል መሳሪያ ነው"። በማለት ገልጸውታል። ምንም አንኳ የመጻፍ ክሂል ጥቅሙ ከፍተኛ ቢሆንም ተግባራዊ ልምምዱ በተማሪዎች ዘንድ አዳጋች ሆኖ ይታያል። Richards(1990:100) እንደገለጹት ጽህፈትን በወጉ መማር ኣሰልቺ እና የረጅም ጊዜ ልምምድን የሚጠይቅ በመሆኑ ተማሪዎች ጭንቀት እና ተስፋ መቁረጥ እንድሰማቸው ያደርጋል።

የጽህፈት ትምህርት ውስብስብ በመሆኑ ኣብዛሃኞቹ የቋንቋ ተማሪዎች በአፍ መፍቻም ይሁን በሁለተኛ ቋንቋቸው ከስህተት የጸዳ ጽሁፍ መጻፍ አለመቻላቸውን እና ችግሩም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጭምር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን Richards (1990:100) ባየ (1987፡8) እና Nunan(1989:39) ይገልጻሉ። ከችግሮቹ መካከልም ዋና ዋና የሚባሉት የመምህራኑ የማስተማሪያ ዘደ ድክመት፣ የተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎት ማጣት ፣ የተመደበው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ማነስ፣ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ተጠቃሽ መሆናቸውን ተስፋየ(1981) ገልጸዋል።

Nunan(1999:273) ደግሞ “ መጻፍ የተወሰነ የልምምድ ጊዜ የሚቆይ እና የተረጋጋ የማሰላሰልን ብቃት የሚጠይቅ ውስብስብ አዕምሮአዊ ሂደት ነው”።የ Nunan ገለጻ እንደሚያስረዳው የጽህፈት ክንውን ባንድ ጊዜ በቀላሉ የሚለመድ ያለመሆኑ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የሚሄድ መሆኑን ይጠቁመናል። በመሆኑም ጽህፈት በቂ የሆነ ጊዜ የሚጠይቅ እና ጽሃፊው ከመጻፉ በፊት ማሰላሰልን የሚጠይቅ እና በጊዜ ሂደት የሚሻሻል ክሂል እንደሆነ ከምሁራኑ መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጂ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ጽህፈትን መማር ለተማሪዎች ከፍተኛ ችግር ከመሆኑም በላይ የክሂሉ ባለቤት ለመሆን የሚበቁትን በጣም ጥቂቶች እንደሆኑ Richards(1990) ይገልጻሉ ብዙዎቹ ተማሪወችም የመጻፍ ክሂልን ሊደረስበት የማይችል ረቂቅ ጥበብ ኣድርገው ስለሚመለከቱት በሚያድርባቸው ጭንቀት ትምህርቱን ጭራሽ ዳር ሳያደርሱት ይቀራሉ። መጻፍ ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት በተከታታይ መለማመድን የሚጠይይቅ የክሂል ኣይነት መሆኑን Harmer(1993:1) Ur(1996:26) Richards (1990:101) በተመሳሳይ ሁኔታ ሃሳባቸውን ይገልጻሉ። አለም(1992:14) የምሁራኑን በደገፍ “መጻፍ ሃሳብን በትክክል ለማስተላለፍ ከድምጽ ጀምሮ ያሉት ቃላት እና አረፍተ ነገሮች በቋንቋው ስርዓት መሰረት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እና ተቀነባብረው የሚቀርቡበት ነው።” በዚህ መንገድም ሃሳብን ማስተላለፍ እንዲቻል ሰፊ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል። መጻፍ ከተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው በመሆኑም በተደጋጋሚ በሚደረጉ ሙከራዎች ያድጋል፣ ይዳብራል፣ይበለጽጋል በማለት ምሁሩ ይገልትጻሉ።

ስህተት ማለት ከዘወትራዊ ቋንቋ አጠቃቀም በማፈንገጥ የሚቀርብ የቋንቋ ቅርጽ ነው በማለትNorish(1992) ይገልጻሉ።በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በልምምድ ወቅት አፋቸውን በታላሚው ቋንቋ የፈቱትም ሆነ ያልፈቱት የተለያዩ ስህተቶችን ይፈጽማሉ dulay (1982)።

እንደ corder(1967) ገለጻ የስህተት አይነቶች ግልጽ ስህተት እና ስውር ስህተት በመባል በሁለት ይከፈላሉ። ግልጽ ስህተት ማለት በአንድ አረፍተ ነገር ዉስጥ የተፈጸመውን ስህተት አረፍተ ነገሩን በማየት ብቻ የምንለየው ሲሆን ስውር ስህተት ማለት ደግሞ ስህተቱን ለማውጣት አረፍተ ነገሩን በጥልቀት እና በጥሞና መመርመርን የሚጠይቅ የስህተት አይነት ነው።

Norish(1990:06) “የመጻፍ ትምህርት ሂደታው እንጅ ቅጽበታዊ ባለመሆኑ ተማሪዎች ረጅም ጊዜን በመውሰድ ልምምድ ማድረግ ይገባቸዋል።” በማለት የመጻፍ ክሂል ለመዳበር ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን በግልጽ ለማሳየት ችለዋል። አጥኚውም የጽህፈት ክሂል ሂደትን የሚጠይቅ መሆኑን ቢገነዘቢም

በተጨማሪም የአካባቢ ሁኔታ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚዊ እና የማስተማሪያ ዘዴዎች የራሳቸውን ሚና በመጫወት እንዴሁኔታው ልዩነትን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ማስገንዘብ ይፈልጋል። ይህንንም አስመልክቶ ተስፋየ (1986) ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ በተማሪዎች ቁጥር መጨመር እና በትምህርት ክፍለ ጊዚያት መብዛት እየተመካኘ ተማሪዎች የሚጽፉት ነገር ትክክል ይሁን አይሁን ሳይታረም መቅረቱ በጽህፈት ላይ ችግር ያስከተለ ጉዳይ መሆኑ ይገልጻሉ።

በመሆኑም ይህ ጥናትም በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአማረኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስተት ምንጮች በመተንተን የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ያለመ ነው። በጋምቤላ ክልል በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ በጽህፈት ወቅት የሚፈጽሙትን ስህተት የሚያሳይ እስካሁን ድረስ ምንም ኣይነት ጥናት ያልተካሄደ በመሆኑ ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት በማካሄድ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ታሳቢ ያደረገ ነው።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍትኩረት በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የመጃንግ ዞን የጎደሬ ወረዳ የሰሙይ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል የ አማረኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሙዋቸው ስተቶችን እና የስህተት ምንጮች መተንተን ላይ ነው።

አጥኚው ለጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የሆነው ከዚህ ቀደም ሲያስተምር በነበረበት ጊዜያት በመማር ማስተማር ሂደት ተተኳሪ ተማሪዎቹ በሚጽፏቸው ጽሁፎች የሚታዩት የአማርኛ ቋንቋ ህግን ያልተከተለ እና ውስብስብ ችግሮች በማየቱ እና ተማሪዎቹ በቀላሉ የሚፈጽሙትን ስህተቶች ለማረም ባለመቻላቸው የተማሪዎቹን ችግር ለይቶ ለማውጣት እና መፍትሄ ለመፈለግ በማሰብ ነው።

በዚህ የስህተት ትንተና ጥናት ዙሪያ በርካታ ምሁራን ጥናታቸው አቅርበዋል ። ለመጥቀስ ያህልም ልኡል ሰገድ (1999)፣ ምህረት (1998) ፣ ተገኝ (2000)፣ ግርማ (2000)ና መሰረት (2003) ይጠቀሳሉ ። በጥናታቸውም ተጠኝ ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሙትን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች በዝርዝር አቅርበዋል። በመሆኑም ለዚህ ጥናት እንደ መነሻ በመሆን አገልግለዋል። በተጨማሪም ተጠኝ ተማሪዎቹ በድርሰት ጽሁፍ ዉስጥ የሚፈጽሙት ስህተት ምን ምን እንደሆነ ፣ የስህተት ምንጫቸዉንና የስህተት ብዛትና ድግግሞሽን በጥናታቸዉ አቅርበዋል ።

ተገኝ (2000) አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን እና ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማረኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። በጥናታቸው ዉጤትም ስህተቶቹ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰሃሳብ ግንዛቤ እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች መሆናቸው እና የስህተቶቹ ምንጮችም የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳርያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት መሆናቸው ተገልጿል። ይህን የመሰሉ ከከፍተኛ ደረጃ በላይ ያሉ ተማሪዎች ላይ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን በርካታ ናቸዉ ። በመሆኑም አጥኝዉ የድርሰት ጽሁፍ ከሆሄያት ቅርጽ አጣጣልና ድምጸት እንዲሁም የቃላት አጠቃቀም ስለሚጀምር ጥናቶች በትምህርት ቤት በተለይ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ከባድ ስለሚሆን ጥናቱ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቢካሄድ ችግሮችን ገና በእንጭጩ ያስቀራል ብሎ ያምናል ፡ ፡ በመሆኑም በማጃንግ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ ጥናቱን በማካሄድ ለአንባቢያን አቅርቧል ።

### 1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍየሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች በመመርኮዝ ጥናቱን ዳር ለማድረስ ሞክሯል ።

1. በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው?
2. በማጃንግ ቋንቋ አፍ የፈቱ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጫቸው ምንድን ነው?
3. በእያንዳንዱ ድርሰት ዉስጥ የሚገኙ ስህተቶች አይነት እና መጠን እንዲሁም ድግግሞሽ ምን ያህል ነው? የሚሉት ናቸው።

### 1.4. የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጋምቤላ ክልል በማጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ በሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች፣ የስህተቶች ምንጭ እና የድግግሞሽን መጠን መለየት ነው። የሚከተሉት ዝርዝር አላማውችም አሉት።

- በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶችን መለየት
- በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጫቸው ምን ምን እንደሆነ ማሳየት
- በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና መጠን እንዲሁም የድግግሞሹን ብዛት ማሳየት የሚሉት ናቸው።

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

**ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል።አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ያልሆኑ ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርት ውስጥ ለሚፈጽሙት የጽሁፍ ስህተቶች ምን እንደሆነ በማሳወቅ ለአማርኛ መምህራን እገዛ ያበረክታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመጃንግ ቋንቋ አፍ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሙት ስህተት መምህራን ቀድመው ግንዛቤ እንዲሰጡ ይረዳል የሚል እምነት እንዳለ አጥኚው ያምናል በመሆኑም በጋምቤላ ክልል እና አካባቢው በዚህ የጥናት ዘርፍ ለሚሳተፉ አጥኝዎች የመረጃ ምንጭ ዪሆናል ተብሎ ይታሰባል።**

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ትኩረት በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች፣ የስህተት ምንጮች፣ ኣይነት እና መጠን እንዲሁም የድግግሞሽ መጠን መለየት ነው ።ጥናቱ የሚካሄደው በጋምቤላ ክልል በመጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመጃንግ ብሄረሰብ ተወላጅ ተማሪዎች በብዛት ከሚገኙበት ትምህርት ቤት ዉስጥ አንዱ የሆነው የሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነው። በጥናቱም የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲያተኩር በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉትን የመጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎችን ብቻ ፈትሿል። በፍተሻውም ተማሪዎቹ በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስህተቶች ምንጭ ላይ ያነጣጠረ ነው። በመሆኑም አጥኚው በመጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት ያልሆኑ ተማሪዎችን በጥናቱ አያካትትም።

## 1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው

### 1.7.1 ያጋጠሙ ችግሮች

- የጊዜ እጥረት
- የገንዘብ እጥረት
- አማካሪ ጋር በቅርበት ያለመገናኘት

### 1.7.2 መፈትሔዎቻቸው

- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
- ገንዘብን በአግባቡና በቁጠባ መጠቀም
- ከአማካሪ ጋር ያለውን እርቀት በስልክ በመጠቀም የምክር አገልግሎት በማግኘት ጥናቱን አጠናቋል።

## ምዕራፍ ሁለት ፡ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1 የጽህፈት ክሂል ምንነት

ጽህፈት እንደ Byrne (1988:03) አገላለጽ "ጽህፈት ማለትየቋንቋውን የድምጽ ምልክቶች በወረቀት ላይ ማስፈር ነው ሊባል ይችል ይሆናል። ይሁን እንጅ ኣቅናጅቶ ከማስቀመጥ ባሻገር በአእምሮ ያለውን ሃሳብ በጽሁፍ መልክ ኣቀነባብሮ ለአኣንባቢ የመግለጽም ሂደት ጭምር ነው። "በማለት ይገልጻሉ። "ጽህፈት በንግግር ድምጾች በተወከሉ ምልክቶች አማካኝነት ሃሳብን በወረቀት ላይ ለመግለጽ በማስቻሉ ለተማረ ሰው እንደ አንድ ምልክት የሚቆጠር ሰው ሰራሽ መገልገያ ነው።" በማለት Raimes (1983) ይገልጻሉ። Byrne (1988:147) አክለውም ጽህፈት የአንድ ቋንቋ ድምጾችን ከምልክቶቻቸው ጋር እያገናኘን የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው መልኩ በወረቀት ላይ ሃሳቦችን የምናሰፍርበት ክሂል ነው በማለት ይገልጻሉ።

Leki (1990:04) ጽህፈት ማለት የጸሃፊውን ሃሳብ በመረዳት እና ሃሳቡን በ አንባቢያን አእምሮ ዉስጥ ያለምንም ማደናገር መግለጽ ነው።በማለት ይገልጻሉ።ጽህፈት ማለት መግባባት ብቻ አይደለም። ጽህፈት ነገሮችን መገንዘብ፣ መግለጽ እና ማብራራትን ያጠቃልላል።ይህ ማለት በጽሁፍ ኣማካኝነት ሰዎች ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡበት ስሜታቸውን እንድገልጹ ሌሎችን እንዲያግባቡ እና የሌሎች ሰዎችን ሃሳብ ሊቀይር ያስችላል በማለት ያብራራሉ።

ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው ጽህፈት ማለት ምልክቶችን ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን መግባባት መቻልን፣ የጸሃፊያንን ሃሳብ በአንባቢያን አእምሮ ዉስጥ ማስቀመጥ፣ ማብራራት እና ሌሎችንም ማሳመንን የሚያካትት መሆኑን እንረዳለን። እንዲሁም ጽህፈት የንግግር ድምጾችን የሚወክሉ ምልክቶችን በስርዓት አቀነባብሮ ትክክለኛ የሆነ መልዕክትን በወረቀት ላይ በማስፈር ለአንባቢያን ማድረስ እንደሆነ ምሁራኑ ይገልጻሉ።

Zamel(1983:165)"መጻፍ ሃሳብን በሚነበብ መልኩ የማፍለቅ የማደራጀት እና የመግለጽ ሂደት ነው። "በማለት ይገልጻሉ። በተጨማሪም ጽህፈት ጸሃፊው በዙሪያው ያሉትን ክንውኖች በሙሉ ለሌሎች የሚያንጸባርቅበት ሂደት እንደሆነ ጽፏል።አያይዞም ጽህፈት በጽሀፊ እና ባንባቢ መካከል ተግባቦት እንዲፈጠር ስለሚያደርግ እና የተላለፈን ዉሳኔ ሰንዶ ለማስቀመጥ ስለሚጠቅም ለጽሀፊም ሆነ ላንባቢ እውቀትን እንደሚያስገኝ ያስረዳል።

### 2.1.2 የመጻፍ ክሂል አላማ

የመጻፍ ክሂልን የምናስተምርበት ዋና አላማ ተማሪዎች በስልጣኔ እየዳበረ ከመጣው የአለማችን ሁኔታ ጋር ተጣጥመው እንዲሄዱ ለማድረግ ነው። Lee (1997:73-76) "የጽህፈት ትምህርት አላማ ክሂሉን የሚያግዝ እና በተለያዩ የማስተማር ስልቶች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል።" በማለት ገልጸዋል። ተማሪዎች እንዲጽፉ ማድረግ ሁለት አላማዎች አሉት እነሱም ጽህፈትን በተናጠል ማጎልበት እና እግረ መንገዱን ለመጻፍ የሚያግዙ ሌሎች ክሂሎችን ማዳበር ናቸው። የመጀመሪያው አላማ ራሱን ጽሁፉን እንዲችሉ ማድረግ ነው። የጽህፈት ክሂል ያለልምምድ የማይገኝ በመሆኑ ለተከታታይ ክህሎትነቱ ተማሪዎች እንድያዳብሩት እና እንዲማሩት በህይወት ዘመናቸውም እንዲገለገሉበት ማስቻል ነው በማለት baskoff (1972:29) ገልጸዋል። ሁለተኛው የመጻፍ ክሂል አላማ ለሌሎች ክሂሎች መዳበር ጋር ሆኖ ማገልገሉ ነው። የመጻፍ ክሂል ለሌሎች ክሂሎች ማዳበሪያ እና ማጠናከሪያ ይሆናል። "ለመጻፍ ማዳመጥ ለመጻፍ መናገር፣ ለመጻፍ ማንበብ አስፈላጊ ናቸው ። " በማለት White (1980:16) ገልጸዋል።

### 2.1.3 የጽህፈት ክሂል ጠቀሜታ

ጽህፈት ለተማሪዎች ማንኛውንም የትምህርት አይነት ለመማር ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም መምህር ሲያስተምር ማስታውሻ ለመያዝ፣ የሚሰጡትን የክፍል እና የቤት ስራ ለመስራት፣ ከተለያዩ እውቀቶች ለማስታውሻ ለመያዝ እና ሃሳባቸውን ለመያዝ በፈለጉት መንገድ ለመግለጽ የጽህፈት ችሎታ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ ይህን ችሎታ ለማዳበር የተለያዩ ድጋፎችን እና እርማት መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።ጽህፈት በግለሰብ ደረጃ ጽሁፍን ማስታውሻ ለመያዝ ፣ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመመዝገብ፣ መልዕክትን ለመላክ፣ ደብዳቤ ለመጻፍ ፣የዉሎ ማስታወሻ ለመያዝ እንደሚጠቅም ይታወቃል። ተማሪዎች አብዛሃኛውን ጊዜ ጽሁፍን የሚጠቀሙት የቀለም ትምህርትን ለመማር ነው እንደ Hedege (1998) አገላለጽ ጽህፈት ቋንቋ ትምህርት ዉስጥ እንደ አንድ እውቀት ማግኛ ይወሰዳል።ለምሳሌ መዋቅርን እና አዳዲስ ቃላትን ለተማሪዎች ለማስረዳትበጽሁፍ ሊቀርብ ይችላል። የቀለም ትምህርት ለመማር እና ክህሎትን ለማዳበር ከፍተኛ ጥቅም አለው። ከዚህም በተጨማሪ ለንግግር እንደመሳሪያ በመሆን ያገለግላል በማለት ያብራራሉ።

### 2.1.4 የጽህፈት ክሂል ማስተማር

የጽህፈት ክሂልን ለማስተማር አንድ ወጥ እና ምርጥ ዘዴ ይህ ነው ብሎ ለማለት አስችጋሪ መሆኑን የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ጠቁመዋል። Weigle (2002) ሲያብራሩ የጽሁፉን ክሂል ለማስተማር ትምህርቱ እንደሚሰጥበት አውድ የተለያዩ ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ባህላዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ስነልበናዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኣካባቢያዊ ሁኔታዎች የየራሳቸው ተጽዕኖ እና ሚና ያላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህን ዘዴ ብቸኛ እና ተመራጭ ያደርገዋል ለማለት ያስቸግራል በማለት ገልጸዋል። ነገር ግን አብዛኛው የሚስማሙባቸው እና የሚቀበሏቸው አቀራረቦች እና ዘዴዎች የሉም ማለት አይደለም። በእርግጥ የተጠቀሱት ሁኔታዎች በዘመን እና በቦታ ልዩነቶች ዉስጥ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጥሩነታቸው ጎልቶ እንዲወጣ ካልሆነም እንዲወርድ ማድረጋቸው አይቀሬ ነው ሲሉ Yan (2005) ገልጸዋል። በዚህ የተነሳ በየዘመኑ በነበሩ አብዛሃኛው የወቅቱ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነት የነበራቸው በወቅቱ ሲማሩ ከነበሩት ተማሪዎች ማንነት እና አጠቃላይ ከዳራ አኳያ የየዘመኑ ፍልስፍናዎች እንደነበሩ እና የጽህፈት ችሎታ ማስተማሪያ ተመራጭ ዘዴወችም ሆነው ጥቅም ላይ የዋሉ ነበሩ በማለት Richards (1990) እና Nunan(1989) ይገልጻሉ።

Weigle(2002) በቀደምት ኣስር አመታት ዉስጥ የተለያዩ የጽህፈት ችሎታ ማስተማሪያ ስልቶች በተግባር ላይ መዋላቸውን ገልጸዋል። በነዚህ ኣቀራረቦች ላይ ግን እስካሁን  የዘለቁ ዉይይቶች እና ክርክሮች መቀጠላቸውን አስረድተዋል።ጽህፈትን ለማስተማር ጥቅም ላይ ከዋሉት እና በተለያዩ ምሁራን ከቀረበኡት ሃሳብ መሃል በአንጻራዊነት ሲቃኝ የቅርብ ጊዜያት አቀራረቦች ሊባሉ የሚችሉትን በ Bajer and white(2000) ጥናት ውስጥ ማየት ይቻላል። እንደምሁራኑ ኣባባል አራት የአቀራረብ ሂደቶች ተለይተው የቀረቡ ሲሆን እነሱም ውጤት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ /product focused approach/፣ ሂደት ተኮር የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ /process focused approach/ ፣ ዘርፋዊ አቀራረብ/genre approach/ እና ሂደታዊ የዘርፍ አቀራረቦችን / process genre approach/ የሚሉ ናቸው። ይሁንና እነዚህ ዘዴዎች ከትችት የጸዱ ነበር ማለት አይቻልም። በመሆኑም በምንነታቸው ባተገባበር ሂደታቸው እንድሁም በጥንካሬዎቻቸው እና ባሉባቸው እጥረቶች ላይ በተለያዩ ምሁራን አስተያየት የተሰነዘረባቸው ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎችም ሆኑ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎች ከስህተት የጸዱ አለመሆናቸው እና የሃሳብ ተቃውሞ እንዳላጡ ከተሰጡ ስተያየቶች መረዳት እንችላለን። አጥኚውም የተረዳው የትኛውንም የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ብንጠቀም ተማሪዎች ከስህተት የጸዱ ይሆናሉ ተብሎ

ኣይታሰብም። የስህተቱ ብዛት የመቀነስ ሁኔታ ይታይ እንደሆነእንጂ። ምክኒያቱም ጽህፈት ባንድ ጊዜ የሚስተካከል አለመሆኑ እና ሂደት የሚፈልግ ክህሎት እንደሆነ አስረግጦ መናገር ይቻላል።

## 2.2 የስህተት ምንነት

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በጽሁፍ ሃሳባቸውን እንድገልጹ ልምምድ ያደርጋሉ። በዚህ ልምምድ ወቅት አፋቸውን በታላሚው ቋንቋ የፈቱትም ሆኑ ኢ አፍ ፈት የሆኑት የተለያዩ ስህተቶችን ይፈጽማሉ። ነገር ግን ስህተቶቹ ለተማሪዎቹ የቋንቋ እድገት አስተዋጾ የሚያደርጉ እንጅ የውድቀት ምልክት እንዳልሆኑ የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ይገልጻሉ (Littlewood 1984) ። በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ከ አንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ የሚታዩ ስህተቶች በቋንቋው የጽህፈት ህግ ተቀባይነት የሌላቸው የቃላት፣ የሆሄያት እና የአረፍተ ነገር መዋቅሮች መጠቀም እንደሆነ Norish (1983:127) ገልጸዋል። በሌላ ሁኔታ ደግሞ ስህተቶቹ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ የሚችሉ መሆናቸውን Brown (1994:205-206) ገልጸዋል። ይሄውም ግድፈት እና ስህተት በማለት ከፍለውታል። የተማሪዎችን ችሎታ በተገቢ ሁኔታ መተንተን ካስፈለገ በስህተት እና በግድፈት መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ማጤን እንደሚገባ ይገልጻሉ።

ግድፈት የሚወክለው በአፈጻጸም ችግር የሚከሰት ስህተትን ሲሆን በይሆናል በግምት እና በማዳጥ (laps) የሚፈጠር ስህተትም በዚህ ውስጥ የሚካተት ነው። እንደ ብራውን ገለጻ ግድፈት በማንኛውም ሰዓት የሚፈጸም አፈ ፈት እና ኢ አፍ ፈትን የማይለይ ነው። አፍ ፈት ተናጋሪዎች ይህን ማዳጥ ወይም ግድፈት ወድያው ተገንዝበው ሊያስተካክሉት ይችላሉ። ስለዚህ የአፍ ፈቶች የብቃት ችግር ሳይሆን በአፍልቆት ሂደት የተከሰተ ክፍተት ማመልከቻ ነው ። ይህ ክፍተትም ምናልባት በጭንቀት፣ በአፍ ማዳጥ፣ በዘፈቀዳዊ የቋንቋ አጠቃቀም እና የጊዜ እጥረት ምክንያት የሚከሰት ነው።

Little wood (1986) እና Norish (1983) እንደገለጹት ስህተት የመማር ሂደት አንዱ አካል እና ትምህርቱንም በንቃት ለማካሄድ ጠቃሚ ምልክት ነው ። ስህተት ቀደም ሲል በልማዳዊ ሁኔታ በተለያዩ ምልክቶች ቃላትን በማጥበቅ በንቃት ባለመከታተል ወይም በእውቀት ማነስ ከትክክለኛው የቋንቋ አጠቃቀም ማፈንገጥ እንደሆነ እና በተማሪዎች ዘንድ እንደ ውድቀት የሚቆጠር በምሁራኑ ችሎታ ላይም ጥያቄን የሚፈጥር እንደነበረ ይነገራል ። ሆኖም ግን በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ በተካሄደ ምልክታዊ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከታላሚው ቋንቋ አገባብ አለማፈንገጥም ስህተት

ላለመፈጸም ዋስትና ሊሆን አይችልም ። በእያንዳንዱ የቋንቋ ተማሪ የሚፈጸሙ ስህተቶችን የተማሪው የቋንቋ እድገት አመላካቾች እንደሆኑ ተደርገው መቆጠር ያለባቸው ናቸው በማለት ምሁራን ይገልጻሉ።

እንደ Corder (1967:156-161) ገለጻ የስህተት አይነቶች ግልጽ ስህተት እና ስውር ስህተት በመባል በሁለት ይከፈላሉ። ግልጽ ስህተት ከስሙ እንደምንረዳው በአንድ አርፈተ ነገር ዉስጥ የተፈጸመን ስህተት አረፍተ ነገሩን በማየት ብቻ የምንለየው የስህተት አይነት ነው። ስዉር ስህተት የሚባለው ደግሞ እንደ ግልጽ ስህተት አረፍተ ነገሩ በማየት ብቻ የሚለይ ሳይሆን ስህተቱን ፈልፍሎ ለማውጣት ወይም ለማውቅ አረፍተ ነገሩን በጥልቀት እና በጥሞና መመርመርን የሚጠይቅ የስህተት አይነት ነው።

እንደ Norish (1992) አመለካከት ስህተት የሚባለው ከዘወትራዊ የቋንቋ አጠቃቀም በማፈንገጥ የሚቀርብ የቋንቋ ቅርጽ ነው ። ስህተት በተለምዶአዊ የቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ ያፈነገጠ ቢሆንም ስርአታዊ ነው ። በተጨማሪም Corder (1974) እያንዳንዱ ስህተት ለመፈጠር በስተጀርባው ስርአታዊ ምክንያት አለው ይላሉ ይህ ሃሳብ በግንዛቤ ችግር፣ ከድካም እና በጭንቀት የተንሳ ስህተት ሊፈጠር ይችላል ። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የሚፈጸም ስህተት ግድፈት እንለዋለን ። መጀመሪያ ግድፈት የፈጸመው ሰውም ቢሆን እንኳን ድጋሜ ያን ላይፈጽም ይችላል ። በሌላ መልኩ Dulay (1982) እንደሚሉት ስህተት የታላሚውን ቋንቋ ስራአት በአጋባቡ ካለመረዳት ሊመነጭ ይችላል። በዚህ የተነሳ የቋንቋ ታላሚው ስራአታዊ በሆነ ሁኔታ ሊሳሳት ይችላል ይህም ማለት ተማሪው እስኪታረም ወይም አፍ ፈት ተናጋሪዎች እንደዚያ እንደማይሉ እስኪገነዘብ ድረስ ትክክል ነው ብሎ በስህተቱ የቀጥላል። አንዳንድ ጊዜ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች አንድን ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶችም የተለያየ ስህተቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉ ከነዚህ ስህተቶችም በተማሪዎቹ የንግግር ቋንቋ ወይም የጽህፈት ቋንቋ ላይ በሚታዩ እና ተማሪው በታላሚው ቋንቋ በመናገርም ወይም ለመጻፍ በሚያፈልቅበትም ጊዜ ከስነ ድምጽ፣ ከሰዋሰው፣ ከቃላት እና አጻጻፍ ያፈነገጡ ሲሆን ስህተቶች አገባባዊ፣ ሰዋሰዊ አጻጻፍ እና የአጠቃቀም ስህተቶች ናቸው ። ስለሆነም አንድ አንባቢ ወይም አድማጭ እንዚህን ስህተቶች የሚገነዘብባቸው ከታላሚው ቋንቋ ስነልሳንያዊ ህግ የተለያዩ መሆናቸውን ነው።

ይህንን አስመልክቶ Nagara (1983) ተማሪዎች ይሳሳቱታል ነገር ግን ከስህተት ከግድፈትም ጎራ ሊመደቡ የማይችሉ የስህተት አይነት አሉ። የዚህ አይነት ስህተት በየትኛውም ስፍራ በማናቸውም ጊዜ እና ሰዓት ሊከሰት የሚችል ነው። እንዲህ አይነቱን ስህተትም ማዳጥ (laps) ብለን እንጠራዋለን ይላሉ። የማዳጥ

ምክኒያቶች በርካታ ሲሆኑ ከንዚህም መካከል አካላዊ ወይም አዕምሮዊ ድካም፣ ትኩረት ማጣት፣ የትውስታ ማነስ እንዲሁም ብስጭት እና መጠጥ ሊሆኑ ይችላሉ ። የማዳጥ አብይ እና መሰረታዊ መለያ ባህሪውም ስህተት ፈጻሚው ያለምንም ዉጫዊ እርምት ጽሁፉን ወይም ንግግሩን ራሱ ሊያርመው መቻሉ ነው።

## 2.2.1 የስህተት ትንተና አስፈላጊነት

የስህተት ትንተና የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት ። Norish (1992) እንደገለጹት መምህራን ስለሚያጋጥማቸው አዳድስ ተማሪዎች ዳራዊ እውቀት ለማወቅ ማገዝ፣ መምህራን አድስ ክፍል በገቡ ቁጥር የስህተት ትንተና ለማድረግ ከቻሉ ስለተማሪዎቻቸው ዳራዊ ዕውቀት መረጃዎችን በማግኘት የትኛውን ይዘት በምን አይነት መልኩ እና ለምን ያክል ጊዜ ማስተማር እንዳለባቸው እንዲወስኑ ያግዛል ። በዚህም የተማሪዎችን ችግር በሚፈታ መልኩ የተደራጀ የማስተማር ሂደት እንዲኖር የሚያደርግ ነው ። በሌላ መልኩ የስህተት ትንተና በአንድ ክፍል ዉስጥ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ካሉ በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ሂደታቸው ላይ ለየትኞቹ ተማሪዎች የተኛውን የቋንቋ ክሂል አስቸጋሪ እንደሆነ ለመረዳት ያግዛል።

የስህተት ትንተና የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉጤታማ የሚሆንበትን አቅጣጫ ይጠቁማል ። ይህን ሃሳብ በተመለከተ Richards (1974) እና Ellis (1989) ሲገልጹ ከስህተት ትንተና ዉጤት ግንባር ቀደም ተጠቃሚዎቹ የቋንቋ መምህራን እንደሆኑ ሲገልጹ መምህራኑ የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች ዳራዊ እውቀት እንዲረዱ ያደርጋል። ካገኙትም መረጃ በመነሳት የ-ትኛውን ይዘት በምን አይነት መልክ እና ለምን ያክል ጊዜ ማስተማር እናዳለባቸው እንዲወስኑ ያግዛል። በዚህም የተማሪዎችን ችግር በሚፈታ መልኩ የተደራጀ የማስተማር ሂደት እንዲኖራቸው ያግዛል። የማስተማር ስነ ዘዴው እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ያለባቸውን ችግር እንድፈትሹ ይረዳቸዋል። በሌላ በኩል የቋንቋ ተማሪዎችን ሰዋሰው ለማስተማር ስህተቶችን በማደራጀት እንደመረጃ ሊጠቀሙበት ይችላል። በሁለተኛ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆኑት ደግሞ ተማርዎች ናቸው። ተማሪዎቹ በታላሚ ቋንቋ ያላቸው እውቀት ምን ያክል እንደሆነ በመጠቆም ጠንክረው ቢሰሩ የትኞቹን ስህተቶች በቀላሉ እንደሚያስወግዱ እና በየትኛው የቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተው መለማመድ እንደሚገባቸው ያስገነዝባቸዋል። በተጨማሪም ለመርሃ ትምህርት አዘጋጆች መጽሃፎቻቸውን እና የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ተገልጿል።

## 2.3 የጽህፈት እርማት ስልት

የተማሪዎችን ጽሁፍ ባንድ ጊዜ እይታ ወይም እርማት በትክክል ውጤት መስጠት በጣም አስቸጋሪ ነው ። ምክንያቱም በጽሁፍ ስራ ላይ የሚታዩ የተለያዩ ስህተቶችን በአንድ ጊዜ ነቅሶ ማውጣት በጣም እስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ   የተማሪዎችን ጽሁፍ በምናርምበት ጊዜ ጽሁፉን ቀይ በቀይ ከመቀባት ይልቅ የተለያዩ ምልክቶችን (code) በመጠቀም ማረም ተመራጭነት አለው። ይህም ሲባል የምንሰጠው ምልክት ደካማ ጎን የለውም ማለት አይደለም።

Norish(1990:73_75)  የተማሪዎችን ድርሰት በተማሪዎች ከማሳረም ይልቅ በመምህሩ ቢታረም ተመራጭነት አለው ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ መምህሩለስህተቶች ምልክት መስጠት አለበት ። ለምሳሌ T( tense), WF(word form), WO(word order) S (syntax) A(agreement) V(vocabulary) SP( spelling) P( punctuation) ART( article) ST(style)  ወ.ዘ.ተ. ምልክት መስጠት ይገባዋል ። የዚህ ኮድ ጠቀሜታ ጸሃፊው የሰራውን ስራ ታርሞ በሚመለስበት ጊዜ ተማሪው በቀላሉ ስህተቱን አውቆ ለማስተካከል እና ራሱን ለማረም ከመርዳቱም በላይ መምህሩ ስህተቶችን በቀላሉ ለይቶ ለማውቅ እና ለመገንዘብ ያስችለዋል። በአብዛሃኛው የተማሪዎችን ጽሁፍ በማረም ዉጤት የሚሰጡት መምህራን ናቸው ። ይሁን እና የተማሪዎች ጽሁፍ በመምህራን ብቻ ይታረማል ማለት ግን አይደለም በማለት White (1980:17_18) ገልጸዋል።

### 2.3.1 የጽህፈት እርማት አይነቶች

የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ የጽህፈት እርማት አይነቶች እንዳሉ ገልጸዋል። ዋናዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

#### 2.3.1.1 ሁሉንም ስህተቶች ማረም

ይህ አይነት አስተራረም ጥንታዊ እና ኋላ ቀር ከመሆኑም በላይ የመምህሩን ጊዜ የሚያባክን ነው። የተማሪውንም የጽህፈት ተነሳሽነት ይቀንሳል። Byrne (1988:124) በነጻ የጽህፈት እርማት ጊዜ አራሚው የተማሪውችን ዳራ ማወቅ ይኖርበታል። አራሚው በመጀመሪያ ዙር የሚጻፉ ጽሁፎች ላይ ለተራ ስህተቶች ትኩረት መስጠት የለበትም Heaton (1975:150)።

### 2.3.1.2 የተመረጡ ስህተቶችን ብቻ ማረም

ይህ አይነት የአስተራረም ዘዴ Byrne(1988፥124_125) ሲያብራሩ ተማሪው የጻፈውን ሁሉንም ጽሁፍ ከተለያዩ መመዘኛዎች አንጻር ማረም ሳይሆን ሲታረም የሚገባውን መጀመሪያውንም አራሚው መወሰን አለበት። ሁሉንም አይነት ስህተት የሚያርም ከሆነ ተማሪው ከስህተቱ ለመማር ያስቸግረዋል በማለት ገልጸውታል።

#### 2.3.1.3 ተማሪው ስህተቱን ያርም ዘንድ ጥቆማ መስጠት

ጥቆማ መስጠት ሲባል አራሚው መጀመሪያውኑ ስለሚያርመው የስህተት አይነት ለይቶ ስለሚያውቅ ያንን ስህተት ተማሪው እንዲያስተካክል መጠቆም ማለት ነው። የስህተቱን አይነት ለመጠቆምም መጀመሪያ ለስህተት አይነቱ ልዩ ምልክት መስጠት አለበት። ይህንኑ ሃሳብ  Byrne (1988፥125) ይህ አይነቱ የስህተት እርማት ዘዴ ተማሪው በጻፈው ድረስት ላይ ከስህተቱ ስር በማስመር የተለያዩ የማረሚያ ምልክት በመስጠት ተማሪው ስህተቱን አውቆ እንዲያስተካክል የሚያደርግ የማረሚያ ዘዴ ነው። በመሆኑም ይህ አይነቱ የአስተራረም ዘዴ ተመራጭ ነው በማለት ይገልጻሉ።

#### 2.3.1.3 ተማሪዎችን ለይቶ በማስወጣት ስህተታቸውን እንዲያርሙ ማደረግ

ይህ አይነቱ የስህተት እርማት ዘዴ አብዛሃኛውን ጊዜ የሚተገበር አይደለም ምክኒያቱም ጊዜ የሚፈጅ እና አሰልቺ በመሆኑ ነው ። ከዚህ ይልቅ ተማሪዎች ስህተታቸውን በቀላሉ ተረድተው እንደሚያስተካክሉ ለማድረግ የሚከተሉትን መንገዶች መጠቀም ተመራጭነት እንዳለው Byrne (1988፥126) ያብራራሉ።

***ሀ.*** ተማሪዎች በተሳሳቷቸው ስህተቶች ገለጻ በመስጠት እንዲያስተካክሉ ማድረግ

***ለ.*** ተማሪዎች የተሳሳቷቸውን ስህተቶች በመጠቆም ማስተካከያ መስጠት

***ሐ.*** ስህተቶቹ የመማር ምንጭ እንደሆኑ በማወቅ ተማሪዎቹ የፈጸሟቸው ስህተቶች ላይ በመመርኮዝ ትምህርት መስጠት

ከላይ ከቀረቡት አራት የድርሰት ማረሚያ ዘዴውች መካከል በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዉስጥ አጥኚው የተማሪዎችን ጽሀፈት ለማረም እንደተማሪዎቹ የአጻጻፍ ስርዓት እና ሁኔታ አመቺ ሆኖ ያገኘውን ስህተትን ብቻ መርጦ የማረም ዘዴን ተጠቅሟል። ስህተትን በተመለከተ የሚነሱ የምሁራን አመለካከቶች

ስህተትን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ አተያይ አላቸው። Corder (1967) የቋንቋ ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው ስህተቶችን በተመለከተ የስህተት ትንተናን ጠቀሜታ በሁለት አይነት አመለካከት ወይም የአስተሳሰብ ጎራዎች ይንጸባረቃሉ በማለት ይገልጻሉ። የመጀምሪያው አመለካከት ወይም የአስተሳሰብ ጎራ ፍሱም የሆነ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም ቢቻል ኖሮ ስህተት አይከሰትም ሲሉ ስህተቱ የመጣው ከማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት የመነጨ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ሁለተኛው በስህተት ላይ የሚንጸባረቀው አመለካከት የመጀመሪያውን ሃሳብ በመንቀፍ ስህተት ሊከሰት የሚችለው በተልያዩ ምክኒያቶች ነው። በዚህም መሰረት ፍጹምነት በለሌበት ኣለም ዉስጥ እየኖርን ፍጹም የሆነን ነገር መጠበቅ ስለማይቻል እና ፍጹም የማስተማሪያ ዘዴ መቅረጽ እንደማይቻልም ይገልጻሉ። ከዚህ ይልቅ ሊተገበር የሚችለውን ስህተቶችን የመተንተን ስራ በማከናውን ስህተት ወድፊት እንዳይቀጥል መጣር አለብን ይላሉ(Richards1974)። ይህም የምሁራኑ ሃሳብ ስህተት ሁልጊዜ የሚፈጠር እና ፍጹም ልናቆመው የማንችለው የቋንቋ ትምህርት አንዱ አካል መሆኑን ተረድተን መቀበል አለብን በማለት ገልጸዋል።በተመሳሳይ መልኩ Norish(1992) እንደሚገልጹት ስህተት የተማሪውን የቋንቋ ችሎታ አመላካች እና ተማሪው እንዴት ባለ መንገድ ታላሚውን ቋንቋ እየተለማመዱ አንደሆነ በማሳየት ጠቃሚ በመሆኑ ስህተት እንደማያስፈልግ ስህተት እንደ ነውር የሚቆጠር ሳይሆን በቋንቋ መማር ሂደት አብይ አካል ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ጉዳይ ነው።

ከተዘረዘሩት ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው የቋንቋ መረዳት ሂደት ሙሉ በሙሉ ከስህተት የጸዳ ሳይሆን በተለያዩ ውስጣዊ እና ዉጫዊ ተጽእኖ የተጋለጡ መሆኑ ነው። ይሄውም ተማሪዎች በሚፈጽሙት የተለያዩ ስህተቶች ላይ በመመርኮዝ ከጥናቱ የሚገኘው ዉጤት ለመማር ማስተማር ሂደት መዋል የራሱ የሆነ አስተዋጸኦ ስለሚኖረው ተከታታይ እና ቀጣይነት ያለው ትንተና ማካሄድ ጠቃሚ እና ተገቢ እንድሚሆን ይታመናል።

## 2.4 የስህተት ምንጮች

የጽህፈት ትምህርት ብዙ ልምምድ ስለሚጠይቅ በልምምድ ሂደት ከፊደላት ቅርጽ ጀምሮ እስከ ቃላት አጠቃቀም ድረስ የተለያዩ ስህተቶች ይፈጥራሉ። አንድ ህጻን አፍ መፍቻ ቋንቋውን ሲለምድ ሳይኮላተፍ እንደማይሳካለት ሁሉ ተማሪዎችም የጽህፈትን ክሂል ለመለማመድ መደናቀፋቸው አይቀርም ሲሉ Littewood (1986) ያስረዳሉ። ስህተቶች በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጠሩ የየራሳቸውን መከሰቻ

እና መንሰኤ ያላቸው ክንዋኔዎች ናቸው። ጽህፈትም ተግባር እንደመሆኑ በዚህ ተግባር ልምምድ ላይ የሚከሰቱ ስህተቶች ይኖሩታል።

Norrish(1993:12-15) ስህተቶች ለትምህርት ከሚቀርቡበት ነገሮች ምርጫ፣ ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል በተወሰነ ቅደም ተከተል ከሚቀርበው የማስተማር ትኩረት ፣ በቋንቋው ትምህርት ከሚሰጡ ምሳሌዎች፣ በምሳሌዎች አማካኝነት ከሚደረገው የልምምድ ዉጤት ወይም ተማሪዎቹ እንዚህን የትምህርት መረጃዎች ሲጠቀሙ ከሚኖራቸው የአጠቃቀም ሂደት ሊመጡ ይችላሉ ሲሉ ገልጸዋል። እንደ Dulay.e.t.a.l (1982) በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪዎች በጽህፈት ልምምድ ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክኒያት ይሆናሉ ተብለው የተገመቱ ነጥቦች በተለያዩ ምሁራን ተገልጸዋል። ከተገለጹት ምክንያቶች ዋናዋና ናቸው ብለው ያስቀመጧቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ ዉስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማር ዘዴ ድክመት እንዲሁም የስነልቦና ጉዳዮች ናቸው።

## 2.4.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ

Norish (1992) ቋንቋ የመማር ሂደት የተሞክሮ ወይም የልምድ ስብስብ ዉጤት ስለሆነ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ጣልቃ በመግባት የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል። አዲስ ቋንቋ በምናስተምርበት ጊዜ አዲስ ልምድ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ አሮጌው ልምድ በአዲሱ ልምድ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው ። ምክንያቱም በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የድምጽ አይነቶች በሌላ ውስጥ ላናገኛቸው ይችላል ያን ቋንቋ በምንማርበት ወይም በምንለምድበት ጊዜ ስነ ድምጻዊ ችግር ስለሚያስከትል በአንድ ቋንቋ ዉስጥ ያሉ የአረፍተ ነገሮች መዋቅር በሌላው ላይገኝ ይችል ይሆናል። በመሆኑም በሁለተኛ ቋንቋ ለሚማረው ተማሪ አፉን የፈታበት ቋንቋ መዋቅራዊ ተጽዕኖ ሊያደርስበት የሚችል ነው።

በአጠቃላይ ከነዚህ እውነቶች መረዳት የሚቻለው ከሁለተኛ ቋንቁ ትምህርት ላይ የአፍ መፍቻ ቁንቋ ተጽዕኖ ከዋናዎቹ የስህተት ምንጮች እንደ አንዱ ሊቆጠር የሚገባው ነው። አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በሚሰጠው ቋንቋ በሚማሩበት ወቅት ከመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች መንስኤዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ እንደሆነ በርካታ ምሁራን ሃስባቸውን ሰተዋል። የመጀምሪያው በሁለተኛ ቋንቋ አጠቃቀም ስርዓት ከመልመዳቸው አስቀድሞ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ብቸኛ ልምዳቸው ነው። በመሆኑም ተማሪዎች አፍ የፈቱበትን ቋንቋ ሃሳብ እየወሰዱ

በታላሚው ቋንቋ የሚጠቀሙት ስለሆነ በሚጠቀሙት ወቅት ተጽዕኖው አወንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል።

አውንታዊ የምንለው የታላሚው ቋንቋ እና ተማሪው አፍ የፈታበት ቋንቋ ለትምህርቱ የቀረበው መውቅራዊ ስርዓት ይሆን እና ተማሪው አፉን የፈታበት ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ያፈነገጠ ስለሚሆን ለስህተት ተጋላጭ ይሆናል Norish (1992) ።

## 2.4.2 የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ

እንደስህተት ትንተና አራማጆች እምነት ሌላው የስህተት ምንጭ ነው ተብሎ የተጠቀሰው አሉታዊ ዉስጠ ቋንቋ ሽግግር የሚባለው ነው ።ይህም ተማሪው የቋንቋውን አድስ ስርዓት ከተማረ በኋላ ወደ አጠቃቀም ሲሄድ ዉስብስብ በሆነ ውስጣዊ የቁንቋ ባህሪ የተነሳ የሚፈጠረው ስህተት ነው ። Brown (1994:214) እና Little wood (1986:23) ሲጽፉ በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ የሚፈጠሩ ስህቶች የምንላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሚማሩት ቋንቋ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ባህሪያት የተነሳ የሚፈጠሩ ስህተቶችን ነው። እንዚህ ስህተቶች ምንጫቸው አፍ መፍቻ ቋንቋ አይደለም ታላሚ ቋንቋእንጅ። ተማሪዎች በታላሚ ቋንቋ በከፊል ከመጋለጣቸው የተነሳ ለስህተት ሊዳረጉ ይችላሉ። ተማሪዎቹ የአንድን ቋንቋ ህግ በሚገባ ከተረዱ በኋላ ወደ አጠቃቀም ሲመጡ የተሳሳተ ማጠቃለያ በመስጠት ሊሳሳቱ ይችላሉ ። እንደዚህ አይነቱ ስህተት ከህጻናት ቋንቋ ለመዳ ጋር ሊመሳሰል ይችላል። አሉታዊ የውስጠ ቋንቋ ሽግግር ወይም የተሳሳተ ማጠቃለያ ከሚያመጣቸው ስህተቶች አንዱ አንድን የቋንቋ ቅርጽ ለሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ ለመጠቀም መሞከር ነው ። ለምሳሌ አንድ የ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪ "he went" በማለት ፋንታ "he goed" ብሎ ቢጽፍ ሁሉም የ እንግሊዘኛ ግሶች ወደ ሃላፊ ጊዜ ሲቀየሩ በቃሉ መጨረሻ "ed" ይጨምራሉ የሚል የተሳሳተ ማጠቃለያ የተፈጠረ ስህተት መሆኑን ያሳያል ። (Krashen1987)።

የተሳሳተ ማጠቃለያ ሲባል ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ እየለመዱ ሲመጡ የተማሩትን አድስ ስርዓት መሰረት አድርገው በቋንቋው ለመጠቀም ሲሞክሩ የሚሳሳቱትን ማለታችን ነው።ይህም ቋንቋው በሚጠቀምበት መዋቅር ለሁሉም የማይሰራ ከሆነ ተማሪዎች መዋቅሩን በአጠቃላይ ለቋንቋው የሚሰራ አድርገው ሊጠቀሙበት ሲሞክሩ የሚፈጠረውን ስህተት ያሳያል። Brown (1994:164-165) Littlewood (1986፡23) Norish (1992፡31- 30) እንደገለጹት የቋንቋ ተማሪዎችን ለውስጠ ቋንቋ

ስህተቶች የሚያጋልጣቸው የተሳሳተ ማጠቃለያ ብቻ አይደለም ። ያልተሟላ ትምህርት፣ የተሳሳተ ተዛምዶ እና ቃላትን ያለአጋባብ መጠቀም በውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ለሚፈጠሩ ስህተቶች ምክንያቶች ናቸው።

እንደ Negara (1983:37-40) አገላለጽ ባልተሟላ ትምህርት የሚፈጠር ስህተት ስንል የቋንቋ ተማሪው የቁንቋውን መዋቅር ፣ ቃላት፣ የአገላለጽ ስልት ወይም ሌሎች የቋንቋውን ባህሪያት በከፊል በመማሩ የተነሳ የሚፈጠረውን ስህተት ማለታችን ነው ስለዚህም ተማሪው በቋንቋ የሚገኙትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች እና ምሳሊያዊ አነጋገሮች እንዲሁም ሰዋሰዋዊ ስርዓቶች በከፊል በትክክል በከፊል ደግሞ ስህተት ሲያፈልቁ ይስተዋላሉ በማለት ገልጸዋል።

## 2.4.3. የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማር ዘደዎች ድክመት

አንድን ቋንቋ ለማስተማር የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ወይም መጽሃፍት ፣ መምህር እና የትምህርት ይዘት እንድሁም መምህራን የሚከተሏቸው የማስተማር ዘዴዎችም የስህተት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ በስህተት ትንተና ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ይገልጻሉ።ከምሁራኑ ጥናቶች መገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪው ሊያዳብረው የተነሳው የቋንቋ አጠቃቀም የጽንሰሃሳብ ግንዛቤ ሰበብ ሊሆኑ ከቻሉት ጉዳዮች መካከል ዋናዋናዎቹ በማስተማሪያ መጽሃፍት ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብ፣አደረጃጀት እና መምህራን የሚከተሏቸው የምስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት ተጠቃሽ ናቸው። ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ላይተማሪዎች ስህተት እንድፈጽሙ ከሚያደርጓቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ቋንቋውን የሚማሩበት ደካማ የመማር ማስተማር ሂደት ነው ። ይሄውም በታላሚው ቋንቋ የሚካሄድ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ችግሮች ካሉ ተማሪው ለስህተት ሊዳረግ ይችላል።

ይህን አስመልክቶ Richards (1974) እንደሚገልጹት የቋንቋ መጽሃፍትን በአግባቡ አለማደራጀት እና ትክክለኛ ይዘቶችን ይዞ አለመገኘት ሁኔታ ተማሪዎችን ለስህተት ሊዳረጉ ይችላሉ። ከዚህ አኳያ የማስተማሪያ መጽሃፍት አደረጃጀት እና አወቃቀር እንድሁም መልመጃዎችን ያቀረቡባቸውን ስልቶች የስህተት ምንጮች ሲሆኑ መምህሩ የሚከተለው የማስተማር ዘዴ እና በክፍል ውስጥ የሚያቀርቧቸው መልመጃዎች የስህተት ምንጮች ሆነው ሊገኙ ይችላሉ እነዚህ ሁኔታዎች ባልተሟላ መልኩ ከቀረቡ ወደስህተት ሊመራቸው እንደሚችል ምሁራኑ ያስረዳሉ።

ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች እንደስህተት ምንጭ አድርገን መውሰዳችን ትክክለኛ እና ተገቢ ነገር ነው የሚሉት Norish (1992፡14-15) በዋነኛነት መምህሩ የሚያስተምረው እና ተማሪው የሚጠብቀው ይዘት

የተለያዩ የሚሆኑበት አጋጣሚ መኖሩን ለሚያጤን ሰው እነዚህን ጉዳዮች የስህተት ምንጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይረዳል ይላሉ። በመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎችን ስህተት መቀነስ የሚቻለው ተማሪዎች የሚጽፉትን ክትትል በማድረግ እና ተማሪዎቹ የምፈጽሙትን ስህተቶች እንድለዩ እና እንዲቀንሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይሁንእንጅ ክትትል እየተደረገ እርማት የማይስጥ ከሆነ ስህተቱን እንደትክክል አድርገው ይቆጥራሉ ይህን በተመለከተ White (1994: 109) እንደገለጹት ልምምድ ብቻውን የቋንቋ ችሎታን አያሳድግም ስህተት አየተነተነ የማይታይ ለስህተቱም እርማት ያማይሰጥ ከሆነ የተማሪው የጽህፈት ስህተት ስር መስደዱ ከፍ ሊል ይችላል ። ስህተት ሲታረም እያንዳንዱን መምህሩ ማረም አለበት ሳይሆን ተማሪው ራሱ ማረም ይጠበቅበታል ። ምክንያቱም ተማሪው የራሱን ችግር ራሱ ለይቶ ካወጣ እና በተገቢው መንገድ ካስተካከለ ቋንቋን በተሻለ መንገድ ተረድቶታል ማለት ነው ። መምህሩ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ተማሪው የራሱን ስህተት እንዲያርም ቢደረግ የቋንቋውን የመማር ማስተማር ሂደቱን ስኬታማ ያደርገዋል። ከላይ ከቀረበው ጋር በማያያዝ Raimes (1983:22) ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እርስበርሳቸው ማረም እንድችሉ መምህሩ እድል መስጠት እንዳለበት እና ስህተቶቹ ሊፈጸሙ የቻሉበትን ምክንያት እንዲያውቁ መረዳት እንደሆነ ይገልጻሉ።

Norish (1992፡ 83) በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ የመምህሩ የማስተማር ችሎታ ሊለካባቸው ከሚችልባቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች መካከል የቋንቋ ትምህርቱን ሳቢ እና ማራኪ አድርጎ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል የማስተማር ሂደቱ ዉጤታማ ካልሆነ ተማሪዎች ለስህተት የመጋለጥ እድላቸው ላቅ ያለ መሆኑን ምሁራኑ ይገልጻሉ። እንድሁም የቋንቋ መርሃ ትምህርት የይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ የቋንቋውን ይዘቶች ሙሉ በሙሉ መካተት ወይም አለመካተቱን አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማር ተማሪ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ቀላል አይደልም በማለት ይገልጻሉ።

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው ስህተቶችን የሚፈጠሩት ከመማር ማስተማር አቅም ማነስ ፣ ከመርሃ ትምህርቱ በይዘት አቀራረብ፣ አመራረጥ እና አደረጃጀት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ሊከሰት እንደሚችል ነው። መምህሩ የማስተማር ብቃት የሌለው እና በተሳካ መልኩ ትምህርቱን የምያቀርብ እና በተማሪዎቹ የሚፈጸሙትን ስህተቶች ለመፍታት የሚጥር ከሆነ ከፍተኛ ስጋት ላይ የሚጥል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ስለዚህ መምህራን ቋንቋን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ በመማር ማስተማር ሂደት አወንታዊ እና አሉታዊ ጎኖች እንዳሉት መገንዘብ ይቻላል።

### 2.4.4. ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳዮች

ተማሪዎች በጽሁፍ ስህተት እንድፈጽሙ ከሚያደርጋቸው ነገር አንዱ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ሁኔታ ነው ። በቋንቋ መማር ሂደት ላይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ ያለው በጎ አመለካከት ትምህርቱን በሚገባ እንዲከታተል የመርዳቱን ያክል በቋንቋው እና በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ላይ ያለው አመለካከት አሉታዊ በመሆን ደግሞ ለመማር ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል ። ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ የሚኖራቸው ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ሁኔታ ከቤተሰባቸው፣ ከአካባቢያቸው፣ ከጓደኞቻቸው እና ከተለያዩ ተላዉጦዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ነው። በዚህ ምክንያት ተማሪዎች ለሚጽፉት ጽሁፍ ያላቸው ትኩረት ይቀንሳል። ስህተቱም በአንጻሩ ይጨምራል በማለት Norish (1992፡ 18) ይገልጻሉ ስነልቦናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያዘው ከተማሪዎቹ የግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን ተማሪዎቹ ከክፍል ዉጭ ስላለው ሁኔታ በአዕምሮቸው ውስጥ ይዘውት የሚመጡት ነገር በክፍል ዉስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጋቸው ነው። Norish (1992፡19)።

Dobin & Olshtain (1986:15) እንደጻፉት ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ላይ አሉታዊ አተያይን ከሚፈጥሩ ምክንያቶች አንዱ ከቋንቋው የሚገኘው ጥቅም ነው። በመሆኑም ተማሪው ከቋንቋ ትምህርቱ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ ካሰበ ለቋንቋው አወንታዊ አመለካከት በማዳበር ቋንቋውን ለመማር ያለው ፍላጎት ይጨምራል ። በዚህም የተነሳ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ዉስጥ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ይቀንሳሉ ባንጻሩ ተማሪው ቋንቋውን ከተማረ በኋላ ምንም አይነት ተጨባጭ የሆነ ጥቅም እንደማይገኝ ለቋንቋው ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል። በጽሁፍ ውስጥ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችን ሊጨምሩ ይችላሉ። በአጠቃላይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ አሉታዊ አተያይ ካለው ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው የቋንቋ አጠቃቀም ከሌላው ከቋንቋ ማህበረሰብ ባህል እና ልምድ ጋር የራሱ ባህል እና ልምድ የሚጋጭ ከሆነ ለመማር ውስጣዊ ተነሳሽነት ከሌለው በጽሁፍ እና በንግግሩ ውስጥ ስህተቶች እየጨመሩ መሄዳቸውን መረዳት ይቻላል።

በስህተት ምንጮች ትንተና መላምቶች አራት ዋና ዋና የስህተት ምክኒያቶች ተዘርዝረዋል። ሆኖም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኢ አፍፈት ተማሪዎች የስህተት ምንጭ ላይ በመሆኑ እና እነዚህ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ እና የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ለስህተት ሊዳርጋቸው እንደሚችል ይታመናል። ሌሎችም

የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና ዘዴዎች ድክመት እንዲሁም ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ሁኔታውች ተጽዕኖ ስለምያሳድሩ አጥኚው ከ አራቱም አቅጣጫዎች ጥናቱን ለማየት አቅዷል።

## 2.5 የመጻፍ ክሂል መመዘኛ ነጥቦች

አንድ ጽሁፍ የተዋጣለት ነው የሚባለው ከፊደል ቅርጽ አጣጣል አንስቶ የቃላት መረጣ ፣ የሰዋሰው አጠቃቀም ፣ ተገቢ የስርዓት ነጥብ አጠቃቀም እና የአንቀጽ አወቃቀር ችሎታዎች በአግባቡ ሲካተት ነው። የመጻፍ ክሂል የሰዋሰው አገባብን ጠብቆ ቃላትን በአረፍተ ነገሮች አቀናጅቶ የማቅረብ ችሎታ መኖር ብቻ ሳይሆን ሃሳብን በተገቢው መንገድ በማፍለቅ ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ የማደራጀትንም ችሎታ ይጠይቃል። በመሆኑም Pincas (1982:30) “የማግባባት ብቃቱ ተጠይቃዊ አደረጃጀት፣ በቅርጽ እና ባቀራረቡ፣ በሰዋሰው ቅንብር ደረጃው እና በእጅ ጽህፈት፣ በስርዓት ነጥብ አጠቃቀም መስፈርቶች የመጻፍ ክሂል ሊመዘን እና ሊገመገም ይችላል በማለት ሃሳቡን አጠናክሮታል።” በሌላ በኩል Heaton(1975) የመጻፍ ክሂልን ለመመዘን የሚያስችሉ ነጥቦችም እንደሚከተለው አስቀምጠዋል  እነሱም ትክክለኛ እና ተገቢ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ፣ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መጻፍ፣ሃሳብን ቅደም ተከተላዊ እና ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ መግለጽ፣ ተገቢ የሆኑ የአጻጻፍ ስልቶችን በመጠቀም የአረፍተ ነገርን ትክክለኛ እና አሰካክ የአንቀጽ አወቃቀር ስልትን በመጠቀም መጻፍ እና ጽሁፉ የሚቀርብላቸውን ተደራሲያን በማወቅ ለማስተላለፍ የተፈለገን መልዕክት ተስማሚ የሆኑ በመምረጥ እና ሃሳብን ግልጽ በሆነ መንገድ የመግለጽ ችሎታ ሊታይ ይገባል በማለት ያስረዳሉ ። ባጠቃላይ የመጻፍ ክሂልን ለመምዘን ያስችል ዘንድ ቀጥለውየቀረቡት ነጥቦች ወሳኝ ናቸው።

### 2.5.1 የሰዋሰው ህጎች አጠቃቀም

አንድ ጸሃፊ ሃሳቡን በጽሁፍ አማካኝነት ማስተላለፍ ከፈለገ የቋንቋውን ትክክለኛ ህግ እና ስርዓት ተከትሎ መጻፍ አለበት ። ሰዋሰው እያንዳንዱን ቃላት እርስበእርስ በማቀናጀት ዓረፍተ ነገሮች የሚመሰረቱበት መንገድ ነው። በመሆኑም አንድ ጸሃፊ ሃሳቡን ለመግለጽ ሲፈልግ በሚመሰርታቸው አረፍተ ነገሮች ዉስጥ በባለቤቱ እና ማሰሪያ አንቀጹ መካከል የቁጥር ፣ የጾታ፣ መደብ እና ተሳቢ አመልካች ቅጥያዎች ስምምነት እንዲሁም ትክክለኛ የቃላት አገባብ እና የቋንቋውን ስርዓት ጠብቆ መጻፍ አለበት።

## 2.5.2 የቃላት አመራረጥ

ሃሳብን በጽሁፍ አቅናብሮ ለማቅረብ የምንጠቀምባቸው ቃላት ወሳኝ ናቸው ጽህፈት እንደ ንግግር ወዳውኑ ግብረ መልስ የሚገኝበት ስላልሆነ የሚመረጡት ቃላት ምስል ከሳች፣ ሳቢ፣ ለአውዱ ተስማሚ እና ለዛ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። በመሆኑም አማረ (1986:04) "ቃላት የደርሲ ቀኝ እጅ ናቸው ።ደራሲ ያለ ቃላት ሌላ መሳሪያ የለውም ጥረቱ ሊሳካ የሚችለው ቃላትን በጥበብ እና በጥንቃቄ በመጠቀም ለቋንቋው ውበት ማስገኘት ሲችል ነው።" በማለት የቃላትን ጠቀሜታ አጽንዖት ሰጥተው አብራረተዋል ። ይህም አባባል የሚያስገነዝበን አንድ ጸሃፊ ሃሳቡን በተገቢ መንገድ ለማስተላለፍ ከፈለገ ሲጽፍ የሚመርጣቸው ቃላት ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት የሚመረጡት ቃላት የዘየ ችግር የሌለባቸው፣ እንግዳ ያልሆኑ፣ የማያሻሙ፣ ያልተሰለቹ እና መደበኛነት ያላቸው ቢሆኑ ጽሁፉ ተነባቢነት እንዲኖረ ይረዳል።

## 2.5.3 የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም

ስርዓተ ነጥቦች የጽሁፍ መሪ ምልክቶች ናቸው ። ይህ ሲባል ጽህፈት እንደ ንግግር በተለያዩ የአካል እንቅስቃሴ ምልክቶች ሊታጀብ አይችልም ።መልዕክት ግልጽ ለማድረግ የምንጠቀመው ስርዓተ ነጥቦችን ነው ። አማረ ማሞ (1996:203)" በጽሁፍ ውስጥ የሚገቡ ስርዓተ ነጥቦች እና ምልክቶች ተግባር በጽሁፍ የሰፈረው መልዕክት ያለምንም መድበስበስ በአንድ አፍታ የአገባብ እይታ ለአንባቢው እንዲከሰትለት ማገዝ ነው ።" በማለት የስርዓተ ነጥቦችን ጠቀሜታ ገልጸዋል። ስለዚህ ስርዓተ ነጥቦችን ስንጠቀም በአግባቡ እና በሚፈለጉበት ቦታ ላይ ብቻ መሆን አለበት መምህራን ተማሪዎቻቸውን ሲያስተምሩም ስለስራተ ነጥቦች ምንነት አስፈላጊነት እና አጠቃቀም ጭምር እንዲረዱ በጥልቀት ማሳወቅ ይገባቸዋል። የተማሪውችን የጽህፈት እርማት በሚያደርጉበትም ጊዜ መልሶ ግብረ መልስ ለመስጠት ተማሪወቻቸውን ከስህተቶቻቸው እንዲማሩ ማድረግ መዘንጋት የሌለበት ተግባር ነው።

## 2.5.4 የአንቀጽ አወቃቀር

አንድ አንቀጽ ሃሳብን ለመግለጽ ለማስረዳት እና ለማብራራት በሚያስችሉ ዝርዝር አረፍተ ነገሮች እና በአንድ ዋና አረፍተ ነገር ወይም ሃይለቃል የሚገነባ የሃሳብ ጥንቅር ነው። አንቀጹ አንድ ዋና ሃስብ ብቻ ሊያንጸባርቅ የሚችለው በሃይለቃሉ እና በዝርዝር አረፍተ ነገሮቹ መካከል የሃሳብ አንድነት ሲኖር ነው። በመሆኑም pincas (1982:55)" በአንቀጽ ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር አረፍተ ነገሮች በተገቢው መንገድ እየተያያዙ አንዱን ሃሳብ ሊገልጹ የሚችሉ ሊሆን ይገባል።" በማለት ሃሳቡን ያጠናክሩታል ። አንድ የተዋጣለት አንቀጽ የአንቀጽ አንድነት ቅንብር እና ተያያዥነት የሚባሉ ሶስት ነገሮችን ማሟላት አለበት።

### 2.5.5 የአንቀጽ አንድነት

የአንቀጽ አንድነት ሲባል በአንቀጹ ውስጥ ባለው መንደርደሪያ አረፍት ነገር ወይም ሃይለ ቃል እና በሊሎች ዝርዝር አረፍተ ነግሮች መካከል የጠበቀ ትስስር አለ ማለታችን ነው ። በአንቀጹ ውስጥ ያሉ ዝርዝር አረፍተ ነግሮች የሚያብራሩት እና የሚገልጹት ስለ ሃይለቃሉ መሆን አለበት ። ከዚህ አኳያ አንድ አንቀጽ ለመመስረት ሲታሰብ በቅድሚያ ሃይለቃሉን ወስኖ መነሳት ለአንቀጽ አንድነት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው Trimmer & James (1988) ያብራራሉ።

### 2.5.6 የአንቀጽ ቅንብር

የአንቀጽ ቅንብር ሲባል በጽሁፍ ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሃሳብ ለማብራራት እና ለማስረዳት የሚያስችሉ ነገሮችን ባህሪ በመረዳት እንደ ክብደት እና ቅለታቸው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በቅደም ተከተል የሚቀርቡበት ስልት ነው ። በአንቀጹ ውስጥ ያለውን መንደርድሪያ አረፍተ ነገሮችን የሚገልጹ እና የሚያከራክሩ ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን በቅደም ተከተል ከክብደታቸው እና ቅለታቸው አንጻር ከአብይ ወደ ንዑስ ወይም ከንዑስ ወደ አብይ እንደሚቀርቡ Raimes (1983) ያብራራሉ።

### 2.5.7 የአንቀጽ ተያያዥነት

አንድን አንቀጽ የሚመሰርቱት አረፍተ ነገሮች እርስ በእርሳቸው የተያያዙ መሆናቸውን ያመለክታል። አንቀጽን ሊመሰርቱ የሚችሉ ዝርዝር አረፍተ ነገሮች እርስ በእርሳቸው በተገቢው አያይዞ እና ተቀናጅተው ለአንባቢ በቀላሉ ሊተላለፍ የሚፈለገውን መልዕክት ሊያስረዳ ይገባዋል። ከዚህም ሌላ በአንቀጹ ውስጥ ያሉ አረፍተ ነገሮች እርስ በእርሳቸው የሚደጋገፉ ቀድሞ የሚመጣው አረፍተ ነገር ለቀጣዩ ፍንጭ የሚሰጥ መሆን እንዳለበት Trimmer & James (1988) ያስረዳሉ ።

### 2.5.8 የሃሳብ አገላለጽ

የተማሪዎች ትልቁ እና ዋናው ችግራቸው የሚጽፉትን አለማወቅ ሳይሆን በአእምሮቸው የሚጉላላውን ሃሳብ በብእራቸው በወረቀት ላይ ለመዝራት ከየት ጀምሬ የት ልሂድ? ከምን ጀምሬ በምን ላጠናቀው? የሚለው የሃሳብ ፍትጊያ ለጀማሪ ተማሪውች ትልቁ ፈተና ነው።

"የጽህፈት ትምህርት ክፍለጊዜ የተማሪዎች ቁናቁና መተንፈሻ ፣ እግራቸውን ማፋተጊያ እና እርሳስቸውን ማኘኪያ የስቃይ ጊዜ ነው ።"በማለት ጽህፈት ምን ያክል ፈታኝ እንደሆነ Hedge (1988:05) ገልጸዋል ። አጥኚው ከላይ የቀረቡት የመጻፍ ክሂል መመዘኛ ነጥቦች የዚህ ጥናት አላማ ከግብ የሚያደርሱ እና በተጠኙ ተማሪዎች የሚጻፉት አንቀጾች ውስጥ የታዩትን ስህተቶች ለማረም እና ውጤት ለመስጠት ተስማሚ ሆነው ያገኛቸውን የመጻፍ ክሂል መመዘኛ ነጥቦች መርጦ የቃላት አመራረጥ ወይም አጠቃቀም ስህተት፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት የሆህያት አጣጣል ስህተት እና መለየት ያልተቻሉ ቃላትን ከግምት በማስገባት ለተተኳሪ ተማሪዎች የተሰጡ የድርሰት ጽሁፍ ፈተነዎችን ለመመዘን ተጠቅመውበታል ። ከላይ የተገለጹት መመዘኛዎች የተመረጡበት ምክንያት የተተኩሪ ተማሪዎችን የአማርኛ ቁንቋ ትምህርት የድርሰት ጽሁፍ ደረጃ ከግምት ያስገባ በመሆኑ ነው ። ይህም አማርኛን እንደሁለተኛ ቁንቋ ለሚማር እና ለአንደኛ ደረጃ 7 ኛ ክፍል ተማሪዎች መስፈርቶቹ በቂ ናቸው ተብሎ በመታመኑ ነው። በተለይ የሆህያት ቅርጽ አጣጣል እና ድምጽት በተጠኝ ተማሪዎች ላይ በበዛት የተገኙ ስህተቶች ናቸው። ይህም የሚያመለክተው አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቁንቋ ለሚማሩ የ1 ኛ ደረጃ ትምህት ቤት ተማሪዎች የቁንቋ ህግጋት እና ሌሎች መስፈርቶች ክብደት ይኖራቸዋል ተብሎ መታሰቡ ነው ። ምክንያቱም የሆህያትን ቅርጽ፣ ድምጽ ፣ እና የቃላት ምስረታ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ በመሆናቸው ነው።

## 2.6 የጽህፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

ጽህፈትን ለማስተማር ሆነ ለመማር አስቸጋሪ እና ከባድ ክሂል እንደሆነ በርካታ ምሁራን ይገልጻሉ (Gere1987: Horn2000: Kellogg & Raulerson 2007) ። በመማር ሂደት ውስጥ አልፈው ክሂሉን በሚገባ ማዳበር የሚችሉት እና ራሳቸውም በትክክል መግለጽ የሚችሉት ተማሪዎች ቁጥር ጥቂት ለመሆኑ ይሄው ከባድነት እንደሆነ ይገመታል Kroll (1991) ። የክሂሉ ከባድነት እና ለኢ አፍ ፈት የቋንቋ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለ አፍ ፈቱም ጭምር በማስረዳት ከላይ የተገለጸውን ሃሳብ ያጠናክራሉ። ጽህፈት በጣም

ውስብስብ እና የተለያዩ የክሂል ችሎታ መኖሩን የሚጠይቅ በመሆኑ ቀላል ተግባር አይደለም ። ጽህፈትን ውስብስብ የሚያደርጉት የሚከተሉትን ዘርፈ ብዙ ተግባራት የሚጠይቅ መሆኑን (Kellogg & Raulerson 2007) ይገልጻሉ። በተመራማሪዎቹ አገላለጽ ጽህፈት የበርካታ ሂደቶች ትስስር እና ቅንጂት የሚጠይቅ በመሆኑ ቅድመ ጽህፈትን፣ መጻፍን ማረምን እና መከለስን ያካትታል ። አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ በርዕሰጉድዩ ዙሪያ ሃሳብ ማፍለቅን፣ አደረጃጀትን እና ሰዋሰዋዊ ህግጋት መጠበቅን ወ.ዘ.ተ ይጠይቃል።

በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የጽህፈት ክሂልን መማር እና ክሂሉን በብቃት ማዳበር አስቸጋሪ የሚያደርጉት ተለውጦዎች በርካታ ናቸው ። ከተለውጦዎቹ መካከል የክሂሉ ውስብስብነት ማለትም አእምሮዊ አካላዊ እና ስራ መሆኑ ከማሰብ ጋር መያያዙ ጸሃፊው ባንድ ጊዜ ለልይ ልዩ ተለዉጦዎች ትኩረት ሰጥቶ እንዲጽፍ የሚጠይቅ በመሆኑ ለመጻፍ ብዙ ጊዜ መፍጀቱ ከከፍተኛ ጥረትና ድካም በኋላ የሚፈለገው ዉጤት የማይገኝበት መሆኑ ዋናዋናዎቹ ናቸው Widdowson (1987); Tsui (1996), Nunan (1989); Byrne (1988) & Fisher (2012) ። የጽህፈት ትምህርትን ከባድ እና አስቸጋሪ የሚያደርጉትን ተለውጦዎች ከጸሃፊው እና ከአንባቢው ግንኙነት ከቋንቋው ስነ ልሳንያዊ ባህሪ እና ከጸሃፊው እውቀት አንጻር በሶስት ዋናዋና ምድቦች ከፍለዋቸዋል። እንሱም ስነልቦናዊ/psychological problem/ አዕምሮዊ ወይም ግንዛቤዊ ችግር/cognitive problem/ እና ስነ ልሳኒያዊ ችግር/linguistic problem/ ብለው መድበዋቸዋል።

## 2.6.1 ስነ ልቦናዊ ችግር

በንግግር ወቅት ተናጋሪ እና አድማጩ ፊት ለፊት በሚደረግ ግንኙነት ሃሳብ ስለሚለዋወጡ የወዳውኑ ግብረ መልስ/immidate feedback/ ያገኛሉ። ሆኖም መጻፍ በግል የሚከናወን ተግባር ከመሆኑ የተነሳ በተግባቦት ጊዜ ፊት ለፊት ግንኙነት የለም። በዚህ የተነሳ ግብረ መልስ የማግኘቱ ሁኔታ የወዳውንነት ባህሪ የለውም። አጋጣሚውም ጭራሽ ላይፈጠር ይችላል። ይህ ደግሞ በጸሃፊው ላይ ውስጣዊ መረብሽን ያስከትላል Richards (1990) ። ከዚህ ጋር ተያዞ የሚነሳው ሌላው ጉድይ መጻፍ አስቸጋሪ ክሂል በመሆኑ ጸሃፊው ብቻውን የሚያከናውነው ተግባር ስለሆነ በስነልቦናው ረገድ ጠንካራ ሊሆን ይገባል Byrne (1988) ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ መጻፍን ትብብራዊ ማድረግ ቢቻልም አብዛሃኛውን ጊዜ ግን መጻፍ አንድ ሰው በአካል ለማያውቀው አንባቢ ሃሳቡን የሚያስተላልፍበት መንገድ ነው። የወዳውኑ ግብረ መልስ ያለማግኘቱ ባህሪ እና አስቸጋሪነቱ በጽሃፊው ላይ የሚፈጥረው ስነልቦናዊ ተጽእኖ ትምህርቱን ከባድ

እንድሆን ያደርገዋል። ሌላው ጸሃፊው መልእክቱን ለአንባቢው በትክክል እንዲደርስ ለማድረግ ካንባቢው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ማስገባት አለበት። ይህ ደግሞ አእምሮአዊ ጫናን ይፈጥራል። Hedge (1998) ከዚህ ሃሳብ በመነሳት የመጻፍ ክሂል በጸሃፊው ላይ በሚፈጥረው ውስጣዊ መረበሽ አንጻር የበኩሉን ጫና እንደሚያሳድር መረዳት ይቻላል።

## 2.6.2 አእምሮዊ ወይም ግንዛቢያዊ ችግር

ማንም ሰው የመጀመሪያ ቋንቋውን ያለምንም ችግር መናገር ሲችል መጻፍ ግን ትምህርት ቤት ገብቶ ይማራል። ጽህፈት የአእምሮ እንቅስቃሴን የሚጠይቅ እና ጸሃፍቱ ስለ መጻፍ የሚኖራቸውን ክህሎት ወይም እውቀት (ሃሳብ ማፍለቅን እና ሃሳብ ማደራጀትን) ማዳበር ጋር ግንኙነት ያለው ተግባር ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሃሳባቺን በአካል ከሌለ እና ለማናውቀው አንባቢ ግልጽ ለማድረግ አረፍተ ነገሮችን እንደት ማደራጀት እንዳለብን መማር የግድ ነው Byrne (1988) ። Hedge (1988) በበኩላቸው የጽህፈት ትምህርት እጅን ዐይንን እና አእምሮን በማስተባበር በተገቢው ትእምርታዊ ወኪሎች አማካኝነት የግል ወይም የጋራ ገጠመኝም የማካፈል ችሎታን የሚጥይቅ ነው። በማለት ለጽህፈት ትምህርት ክንውን አእምሮዊ ችሎታ ያለውን ድርሻ ይገልጻሉ።በ አንጻሩ አእምሮን በማሰራት የሃሳብ እጥረት ወይም የሚጽፉት ሃሳብ ማጣት ማድረግ አለምቻል፣ ሃሳብን በጽሁፍ መግለጽ አለመቻል ለጽህፈት ትምህርት አስቸጋሪነት ከሚጠቀሱ ምክኒያቶች መካከል ናቸው።

## 2.6.3 ስነ ልሳናዊ ችግር

ቃላዊ ተግባቦት የሚመሰረተው በግንኙነት ሂደት ነው ። ተሳታፊዎቹም ግንኙነቱም የሁለትዮሽ እንድሆን የነቃ ተሳትፎ ያደርጋሉ ። ምክኒያቱም ንግግር ድንገታዊ በመሆኑ የአረፍተ ነገሮቻችን መዋቅር ለማደራጀትም ሆነ ለማያያዝ የምንሰጠው የተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው ። የምንናገረውን ነገርም ሰዎች በሚሰጡን ምላሽ ተመርኩዘን ልንደግምላቸው እና ልናብራራላቸው እንችላለን ። ያልተሟሉ እና ሰዋሰዋዊ ትክክለኝነታቸንውን ያልጠበቁ አረፍተነገሮችም ሊቀርቡ ይችላሉ ። በጽሀፍት ጊዜ ግን ተግባቦትን የሚያስቀጥል ሆኖ አናገኘውም ምክኒያቱም በጽሁፍ የሚደረገው ተግባቦት በጸሃፊው እና በአንባቢው መካከል ፊት ለፊት የሚከናወን ግንኙነት ባለመሆኑ በሰዋሰዋዊ ግድፈቶች ምክንያት የሚከሰቱ የመልእክት መዛባቶችን ማስተካከል የሚቻልበት አጋጣሚ ጭራሽ አይኖርም። ስለዚህ በጽሁፍ በሚደረገው ተግባቦት እንዳይደናቀፍ ጸሃፊው የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት ማወቅ ይጠበቅበታል። Byrne (1988)

ይህንን ለማድረግም ረጅም ጊዜ በሚፈጅ የአጻጻፍ ሂደት ውስጥ ማለፍ ይጠበቅበታል ። የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርገውም ይሄው ሰፊ ጊዜን እና ትዕግስትን የሚጠይቅ ሂደትን ማለፍ የሚፈልግ መሆኑ ነው።

Harmer (1991) ስለዚህ በጽህፈት ትምህርት ረገድ የቋንቋውን የአወቃቀር ስርዓት ማወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው ። ምክንያቱም ሃሳብን በጽሁፍ አማካኝነት በትክክል መግለጽ የሚቻለው የቋንቋውን ስርዓት ጠንቅቆ በማውቅ በመሆኑ ነው ። እውቀቱ ደግሞ ስርዓቱ አጠቅቀሙ ጋር በማዋሃድ በጽሁፍ ለመግባባት ያስችላል Byrne (1988) ። ስለሆነም የመጻፍ ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርጉት ባህሪያት በመነሳት ክሂሉን ለማስተማር ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮችን መረዳት ያስፈልጋል። ይሄውም የተማሪውችን ስነልቦና ሁኔታ የእውቀት ደረጃ እና የአእምሮ ብስለታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ለክሂሉ መዳበር የሚቀርቡትን ይዘቶች ተገቢ አቀራረብም ተከትሎ ተግባራዊ ማድረግ እና ተገቢ የግብረመልስ መስጠት አስፈላጊ ነው Byrne (1988)።

## 2.7 ጽህፈትን በማስተማር ረገድ የመምህሩ ሚና

ከጽህፈት ትምህርት የሚጠበቀው አጠቃላይ ግቡ ተማሪዎች ጽህፈትን ከማህበራዊነት፣ በትምህርታዊነት፣ በሙያ እና በሂወት ገጠመኞቻቸው ውስጥ በአግባቡ እንድገለገሉበት ማድረግ ነው ። እነዚህን ክህሎቶች ተማሪዎች በተገቢው መንገድ እንዲያጎለብቷቸው የመምህሩ ሚና ከፍ ያለ ነው Hedge (1988:08)። መምህራን በጽህፈት መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል።

- ✓ በጽህፈት ትምህርት ወቅት ተማሪዎች ሃሳብ እንዲያፈልቁ ማገዝ
- ✓ የጽህፈት ትምህርት ወቅት የጽሁፍ ሞደል ማቅረብ እና የጥሩ ንባብ ልምድ እንድኖራቸው ማበረታታት
- ✓ እቅድ እንዲያወጡ ማገዝ
- ✓ በክፍል ውስጥ ተስማሚ ሁኔታዎችን መፍጠር እና
- ✓ ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የጽሁፍ መልመጃዎችን ማቅረብ ናቸው።

Raimes (1983:12-22) መምህራን ጽህፈትን በሚያስተምሩበት ጊዜ ለራሳቸው ማቅረብ የሚገባቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል።

1. ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በተገቢው መንገድ እንዲማሩ መጻፍ እንዴት ያግዛቸዋል?
2. አመቺ የሆነ ርዕስ እንዴት ማግኘት ይችላሉ?
3. ተማሪዎች የሚጽፉት ዓረፍተ ነገር ትርጉም እንድኖረው እንደት ማገዝ እችላለሁ?
4. ተማርዎች የጻፉትን የሚያነበው ማነው?
5. ተማሪዎች ጽሁፋቸውን እንድጽፉ ምን ያክል ጊዜ መሰጠት አለበት?
6. ተማሪዎች የሚፈጥሩትን ስህተት በተመለከት ምን ማድረግ አለብኝ? የሚሉት ናቸው ።

በሌላ በኩል Richards (2000:111) ጽህፈትን አስመልክቶ መምህሩ ሊያከናውነው የሚገባውን ተግባር እንደሚከተለው ገልጸውታል ።

- የጽህፈትን ሂደት ያስተምራል
- የጽህፈት ተግባራት ግልጽ እና ቀላል ሆነው እንድቀርቡ ያደርጋል
- የጽህፈት ዉጤትን ይተነትናል ይገመግማል
- መልመጃዎችን በተገቢው መንገድ ይደራጃል
- የተማሪዎችን የአጭር እና የረጅም ጊዜ ግብ ያዘጋጃል የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎች በግል እና በቡድን እንዲያከናውኑ እና መጠኑም እንዲጠበቅ ያደርጋል።
- ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን እንድጠቅሙበት ያግዛል
- የሆህያትን አጣጣል የስርዓተ ነጥቦችን እና የአንቀጾችን አደረጃጀት ያስተምራል
- የጽህፈት ህጎችን እና መርሆችን ያስተምራል

በአጠቃላይ መምህሩ የመማር ማስተማሩ ሂደቱን ከመመቻቸቱም በላይ ተማሪዎች ወደተሻለ የጽህፈት ደረጃ ላይ እንድደርሱ ልምዱን የሚያካፍል ሲሆን የተሻለ አቀራረብ እንድኖርም ውይይቶችን ያካሂዳል።

## 2.8 የሃገር ውስጥ ቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ተማሪዎች በጽህፈት ክሂል የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች በተመልከተ በተለያዩ ዘመናት ጥናቶች ተካሂደዋል። ከነዚህ ጥናቶች መካከልም ኢ አፍ ፈት የሆኑ የአማረኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ብቻ ቀርበዋል።

አማረ (1996) አፋቸውን በትግረኛ ቋንቋ የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስነልሳናዊ ስህተቶች በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። በውጤቱም ስህተቶቹ ስነድምጻዊ፣ ስነምዕላዳዊ፣ ስነአገባባዊ እና ስነ ፍቻዊ መሆናቸው ተገልጿል። የስህተት ምንጮቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ የታላዊው ቋንቋ እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተጽእኖ መሆኑ ተገልጿል። የአማረ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች በአንደኛ ደረጃ እና አማርኛን ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት ላይ ትኩረት ማድረጉ ነው።ልዩነቱ የአማረ ጥናት ስነ ልሳናዊ ጥናት ላይ ማተኮሩ ነው።

ልዑልሰገድ (1997) በወላይትኛ እና በሲዳመኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። ጥናቱም ትኩርት የሚያደርገው በስነ ልሳናዊ ስህተቶች ላይ ሲሆን በውጤቱም ተማሪውቹ በድምጽ ፣ በቃላት፣ በሃረግ እና በአረፍተ ነገር ደረጃ ስህተቶችን መፈጸማቸውን ገልጸዋል ለስህተቶቹ መፈጠር በምክኒያትነት የቀረቡትን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ፣የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እን ዘዴዎች ድክመት እንድሁም ስነልቦናዊ ሁኔታዎች ናቸው። የልዑልሰገድ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት ላይ ትኩረት ማድረጉ ነው።እንደ ልዩነት የሚታየው ደግሞ ልዑልሰገድ በወላይተኛ እና በሲዳመኛ በሁለቱም ብሄረሰብ ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በማጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ላይ ብቻ አተኩሯል።

ምህረት (1998) በሀድየኛ ቋንቋ አፈቸውን የፈቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ ዉጤትም ተማሪዎቹ የፈጸሟቸው ስህተቶች የቋንቋ አጠቃቀም የቋንቋ አወቃቀር(የሰዋሰው) የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና ከጽንሰ ሃሳብ ጋር የተያያዙ ስህተቶ መሆናቸውን ያመለክታል።የስህተቶቹ ምንጮችም የውስጥ ቋንቋ ተጽዕኖ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ መሆናቸው ተገልጿል። የምህረት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በሁለተኛ ቋንቋ አማርኛ የሚማሩት ላይ ማተኮሩ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ ይህ ጥናት በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ሲያተኩር የምህረት ጥናት ግን በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው።

ተገኝ (2000) አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን እና ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። በጥናታቸው ዉጤትም ስህተቶቹ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰሃሳብ ግንዛቤ እና

መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች መሆናቸው እና የስህተቶቹ ምንጮችም የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእ፣ የማስተማሪያ መሳርያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት መሆናቸው ተገልጿል። የተገኝ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር  የሚያመሳስለው አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት ላይ ማተኮሩ ሲሆን ልዩነቱ መደግሞ የተገኝ ጥናት  የኮሌጅ ተማሪዎች ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን በአንደኛ ደረጃ ላይ ያተኮረ ነው።

ግርማ (2000) በጌድዖኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶ እና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። በጥናቱ ዉጤትም የስህተቶቹ አይነቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አውቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰሃሳብ ግንዛቤ እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች መሆናቸው እና የስህተት ምንጮቹም የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክምት መሆናቸው ተገልጿል። የግርማ ጥናት ከዚህ ጥናትጋር  የሚያመሳስለው  ከላይ እንደተገለፀውአማርኛን  እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት ላይ ማተኮሩ ነው።  ልዩነቱ በተለያዩ ቋንቋ መጠናቱ ብቻ ነው።

መሰረት (2003) በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፊበት ወቅት የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። በዉጤቱም የስህተት አይነቶቹ የቋንቋ አጥቃቀም የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ፣ የጽንሰሃሳብ ግንዛቤ እና መለየት ያልተቻሉ የስህተት አይነቶች መሆናቸውን ተገልጿል ። ለስህተቶቹ መከሰት ምክንያት የሆነውም የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ በመማር ማስተማር ሂደት፣ በስነልቦናው ሁኔታዎች እና በሌሎች ተጽእኖዎች የተፈጸሙ መሆናቸውን አመልክተዋል። የመሰረት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት ላይ ማተኮሩ ነው። ልዩነቱ ደግሞ የመሰረት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን አንደኛ ደረጃ ላይ አተኩሯል።

ባጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች በተለያዩ ሃገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች በሚለው ርዕስ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል።

ከላይ የተገለፁት ተዛማጅ ጥናቶች አብዛኛው የሚያመሳስላቸው የሁለተኛ ቋንቋቸው አማርኛ የሆኑ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ  የሚፈፅሙት  ስህተቶች  እና የስህት ምንጮች  በሚል የሚመሳሰሉ ሲሆን

ልዩነታቸው ደግሞ በተለያየ ቋንቋ አፍ የፈቱ መሆናቸው በከፍተኛ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ላይ ሲያተኩሩ ከዚህ ጥናት የሚለየው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያልገፉ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ማተኮሩነው።

ይህ ጥናት በአንደኛ ደረጃ ያተኮረበት ምክንያት የድርሰት ፅሁፍ ስህተት በአብዛኛው የሚፈፀሙት በዚሁ የከፍል ደረጃ ላይ መሆኑ እና የበለጠ ትኩረት ሊደረግ የሚገባው ገና የሆሄያት አጣጣል እና ቅርፅ እንዲሁም ድምፀት ባለዩት ላይ ስለሆነ ነው። ይህም ስህተ ትገና በለጋው ካልተቀጨ ወይም እርማት ካልተሰጣቸው የድርሰት ፅሁፍ ስህተቶች ላይ የሚታዩ ክፍቶች እያደጉ የመሄድ እድላቸው ከፍተኛ ነው። በተለይ እዚህ ጥናት ላይ እንደታየው አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በስህተታቸው እንዱቀጥሉ ያደረጋቸው መምህራን በአማርኛ ቋንቋ የሰለጠኑ አለመሆናቸው እና ከ1ኛ-4ኛ ክፍል በትክክል ፊደል ሳይለዩ 5ኛ ክፍል እንደ አዲስ ይጀምራሉ። በዚህም ምከንያት በድርሰት ፅሁፍ ላይ የሚታዩ ስህቶች እየሰፉ እንደመጡ ከመምህራን የተገኙ ቃለ ምልልሶች ምስክር ናቸው። ለዚህም ነው ጥናቱ በአንደኛ ደረጃ ላይ አደርጎ ክፍቱን ለማሳየት የሞከረው ማለት ይቻላል።

# ምዕራፍ ሶስት ፡የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ፣ የስህተት ምንጮች ፣ አይነት፣ መጠን እና ድግግሞሽን ይፈትሻል። በተማሪዎች ድርሰቶች ላይ የሚታዩ የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ለመለየት እና ለመግለጽ አይነታዊ የምርምር ሂደትን እንድሁም የስህተቶቹን መጠን እና ድግግሞሹን ለመለየት ደግሞ መጠናዊ የምርምር ሂደትን ተጠቅሟል።

3.2 የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት በጋምቤላ ክልል በመጃንግ ዞን ጎደሬ ወረዳ ከሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የሆነው ሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ነው ። ትኩረቱም የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን ነው።

3.3 የናሙና አመራረጥ

የናሙና አካላይ የሆኑት በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በመጃንግ ዞን በጎዴሬ ወረዳ ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የሰሙይ ትምህርት ቤት የተመረጠ ሲሆን በትምህርት ቤቱ በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱትን ብቻ ይመለከታል። ይህም የሚሆነው የሰባተኛ ክፍልን ትኩርት በማድረግ ይሆናል ። በጥናቱ የትምህርት ቤቱ የአማረኛ መምህራን የተካተቱ ሲሆን ተማሪዎችን በተመለከት ደግሞ ሃምሳ ሁለት በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል።

3.3.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ ተተኳሪ የሆነው በጋምቤላ ክልል በመጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ ከሚገኙት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ሰሙይ ትምህርት ቤት በተተኳሪነት ተመርጧል ። የተመረጠበት ምክንያት በወረዳው ከሚገኙት በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በብዛት የሚገኙበት በመሆኑ ላጥኚው መረጃ ለማግኘት በአነስተኛ የትራንስፖርት ወጭ በትምህርት ቤቱ በመገኘትመረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ሆኖ

በመገኘቱ በአመቺ ናሙና ዘዴ ተመርጧል ። ይህም የአጥኚውን የገንዘብ አቅም እና የመርጃ ክፍተት ለመሙላት ምቹ ይሆናል ተብሎ ታምኗል ።

### 3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው የክፍል ደረጃ ሰባተኛ ክፍል ሲሆን ይህ የሆነበት ምክንያት በ2015 ዓም ለትምህርት ከተመዘገቡ ተማሪዎች ለመረጃ መሰብሰብ ቁጥራቸው በዛ ብለው የሚገኙት እና በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የሚገኙበት ክፍል በመሆኑ እና ለጽህፈት ትምህርት ጥናት በቂ ይሆናሉ ብሎ አጥኚው በማሰቡ ነው። ይህም የክፍል ደረጃ በአማርኛ ቋንቋ የሚጻፉ ድርሰቶችን ለመገምገም እና የስህተቶችን ምንጮች ለማውቅ እና ለመለየት ተመራጭ በመሆኑ በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተካቷል ።

### 3.3.3. የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚካሄደው በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በመጃንግ ዞን ጎደሬ ወረዳ በሚገኘው የሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን የተመረጡትም የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው ። የ2015 ዓ.ም የሰሙይ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ወንድ =20 ሴት =30 በድምሩ 50 ተማሪዎች ናቸው ። ይህም ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ተወስደዋል ።

### 3.3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄድው በሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በትምህርት ቤቱም ሁለት ብቻ የአማረኛ መምህራን ይገኛሉ። በመሆኑም በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በጥናቱ አካቷል።

## 3.4 የመረጃ መስብሰቢያ መሳሪዎች

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተብለው የተመረጡት ተማሪዎች የሚጽፉቸው ድርሰቶች፣ በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ እና ለመምህራን የሚቀርቡ ቃለ መጠይቆች ናቸው። ወሳኝ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚሆነው የተተኳሪ ተማሪዎች ድርሰቶች ናቸው ። ይህም የስህተት ምንጮችን ለመለየት እና ተማሪዎች የሚፈጽሙትን የስህተታቸዉን ምንጭ ምን እንደሆነ ለማወቅ ከመጥቀሙም

በላይ የስህተቱን መጠን እና የድግግሞሹን መጠን ለመመርመር የሚያችሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። የጽሁፍ መጠይቁ ተማሪዎቹ ከድርሰት ጽሁፍ ጋር በቀጥታ ሊገናኙ የሚችሉ ችግሮችን ፍንጭ ሊሰጡ ይችላሉ የሚል ግምት በመኖሩ ነው ። የመምህራን ቃለ መጠይቁ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ያልተገኙ እና የጎደሉ መረጃዎችን ለመሙላት ተጠቅሞበታል።

### 3.4.1 ድርሰት መጻፍ

ጥናቱ በመማር ላይ ያሉ የሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አፋቸውን በመጃንግ ቋንቋ የፈቱ 50 የተመረጡ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ድርሰት እንድጽፉተደርጓል።ተተኳሪ ተማሪዎችን ድርሰት ለማጻፍ በአጥኚው የተዘጋጁ እና በሁለት የአማርኛ መምህራን የተገመገሙ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ ባህል እና የአኗኗር ሁኔታን መሰረት ያደረጉ ሁለት ርዕስ በመስጠት ድርሰት እንዲጽፉ ተደርጎ ጥናቱ ተካሂዷል።

### 3.4.2 የጽሁፍ መጠይቅ

በተተኳሪ ተማሪዎች የሚሞላ በክፍት መልክ የተዘጋጁ የጽሁፍ መጠይቆች በማቅረብ ተማሪዎች ከጽህፈት ክሂል አተገባበር ጋር የሚነሱ ችግሮች ካሉ እና የግል አመለካከቶችን የሚያንጸባርቁ መረጃዎችን እንዲሰጡ ታስቦ የሚቀርብ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው።

ለጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ወንድ=20 ሴት=30 በድምሩ 50 ተማሪዎች በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጥው የጽሁፍ መጠይቅ ይቀርብላቸዋል። የጽሁፍ መጠይቁ የሚቀርበው ከድርሰት ጽሁፍ ጋር ወይም በጽህፈት አተገባበር ላይ ለሚነሱ ችግሮች ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸው መረጃዎችን ለማግኘት በማሰብ ነው ። በመጠይቁም ከጥናቱ አላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሃሳቦች ያሉበት መጠይቆችን በማቅረብ መረጃ ሰብስቧል የተገኙ መረጃውችንም በመጠናዊ እና አይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ በመጠቀም አቅርቧል።

### 3.4.3 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቁ በሰሙይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚገኙ የአማርኛ መምህራን የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሲሆኑ የመምህራኑ ብዛትም ሁለት ብቻ በመሆኑ በጠቅላይ ናሙና የተመረጡ ሲሆን ቃለ መጠይቁ ያስፈለገው በድርሰት ጽሁፍ እና በጽሁፍ መጠይቁ ያልተገኙ መረጃዎችን ክፍተት ለመሙላት ታሳቢ ያደረገ ነው። የተገኙትንም መረጃዎች በአይነታዊ እና በመጠናዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ በመጠቀም አጥኚው መረጃውን በማዘጋጀት አቅርቧል።

3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ድርሰት መጻፍ፣ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ አጥኚው የመረጃ መሳሪያዎችን በአግባቡ በመጠቀም የሰበሰባቸውን መረጃዎች በአይነታዊ የመርጃ መተንተኛ ዘዴ እና መጠናዊ የመረጃ ዘዴን በመጠቀም ለተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈጸሙትን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች በመለየት ተንትኗል።

በጥናቱ በተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህተቶችን ለመለየት እና ለመተንተን በNorrish (1992) የቀረበውን የስህተት ትንተና ዘዴ ተጠቅሟል ። ይሄውም የስህተት አተናተን ቀመር የሚከተለው ነው።

3.6 ጥናቱ የተጠቀመባቸው የስህተት አተናተን ቀመር

$$\text{አማካይ የቃላት ብዛት} = \frac{\text{የቃላት ብዛት}}{\text{የድርሰት ብዛት}}$$

$$\text{አማካይ ስህተት} = \frac{\text{አጠቃላይ ስህተት ብዛት}}{\text{አጠቃላይ ድርሰት ብዛት}}$$

$$\text{የስህተት ድግግሞሽ} = \frac{\text{አማካይ ስህተት} \times 100}{\text{አማካይ የቃላት ብዛት}}$$

$$\text{የትክክለኝት ተዛማጅነት} = \frac{\text{አጠቃላይ የቃላት ብዛት}}{\text{አጠቃላይ የስህተት ብዛት}}$$

ከላይ እንደተገለጸው በአንድ ድርሰት ውስጥ በአማካይ ምን ያክል ቃላት እንዳሉት ለማወቅ የአንድ ድርሰት አማካይ የቃላት ብዛት =ቃላት ብዛት ሲካፈል ለድርሰት ብዛት፣ የአንድን ድርሰት አማካኝ ስህተቶችን ለማወቅ አማካኝ ስህተት = አጠቃላይ ስህተት ብዛት ሲካፈል ለአጠቃላይ ድርሰት ብዛት ፣ በመቶ ቃላት አንድ ስህተት የሚፈጸምበትን መጠን ለማወቅ የስህተት ድግግሞሽ = አማካኝ ስህተት × 100 ሲካፈል

ለአጠቃላይ ቃላት፣ አንድ ስህተት የሚገኝበትን የቃላት ብዛት ለማውቅ የትክክለኝነት ተዛማጅነት= አጠቃላይ የቃላት ብዛት ሲካፈል ለአጠቃልቅይ የስህተት ብዛት ይሆናል።

ከላይ በቀረብው ትንተና ቀመር መሰረት ትንተናው ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በጥናቱ ሪፖርት ቀርቧል ። የጽሁፍ መጠይቁንም ሆነ የቃለመጠይቁን ዉጤቶች ወይም መረጃዎች በቅደም ተከተል በጥንቃቄ በማዘጋጀት በአይነታዊ እና የመጠናዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም ጥናቱን አቅርቧል ።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና እና ማብራሪያ

### 4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው በመጃንግ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሰባተኛ ክፍል የሰሙይ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች መለየት እና የስህተት ምንጮችን መጠቆም እንድሁም የመፍትሄ ሃሳብ መስጠት ነው ። የጥናቱ አጠቃላይ አላማም በምዕራፍ አንድ ላይ ለተነሱ መሪ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል ። መሪ ጥያቄዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

1. በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው?
2. በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጫቸው ምንድነው?
3. በእንዳንዱ ድርሰት ውስጥ የሚገኙ ስህተቶች አይነት እና መጠን እንድሁም ድግግሞሽ ምን ያህል ነው? የሚሉት ናቸው። በመሆኑም ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች ፣ ለተማሪዎች ከተሰጡ የጽሁፍ መጠይቆች እንድሁም ከሰሙይ ትምህርት ቤት የአማርኛ መምህራን ጋር በተደረጉ ቃለ ምልልሶች በቅደም ተከተል በዝርዝር ቀርበዋል።

#### 4.1.1. **በድርሰቶች ውስጥ የታዩ ስህተቶች**

ከላይ በርዕሱ እንደተገለጸው ተማሪዎች ከጻፏቸው የድርሰት አይነቶች ውስጥ የታዩ ስህተቶች በዝርዝር ቀርበዋል። በዝርዝር የቀረቡትም የሆህያት ስህተቶች ፣ የስርዓተ ነጥብ ስህተቶች፣ የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶችን ነው። ሌሎች ስህተቶች ከተማሪዎች የአማምርኛ ቋንቋ የድርሰት ጽህፈት ዝቅተኝነት አንጻር ሊታይ አልቻለም።

ሰንጠረዥ 1 የድርሰት ስህተቶችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የድርሰት አይነት | የድርሰት ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ብዛት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የትክክለኝ ነት ተዛማጅነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አንድ | 50 | 2510 | 50.2 | 1455 | 57.9 | 29.1 | 57.9 | 1.7 |
| ሁለት | 50 | 3080 | 61.6 | 1440 | 46.7 | 28.8 | 46.7 | 2.1 |
| አንድ እና ሁለት | 100 | 5590 | 55.9 | 4595 | 82.2 | 45.9 | 82.2 | 1.2 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በሁለት ዙር 100 ድርሰቶች እንድጽፉ ተደርጓል። ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በ5590 ጠቅላላ ቃላት ውስጥ ያሉት ስህተቶች ተለይተው ተቆጥረዋል ። ከተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ ያሉት አማካይ ቃላትም 55.9 ነው። ተማሪዎቹ ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የመጀመሪያው ድርሰት ውስጥ 2510 የቃላት ብዛት ሲኖር አማካይ ቃላት ደግሞ 50.2 ነው። የስህተት ብዛቱን ስናይ ደግሞ 1455 ነው። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 57.9 ይሆናል። አማካይ ስህተቱ ደግሞ 29.1 የስህተት ድግድሞሹ 57.9 የትክክለኘት ተዛማጅነት ደግሞ 1.7 ሆኗል።

በሁለተኛው ድርሰት ውስጥ ደግሞ አጠቃላይ ቃላት 3080 ሲሆን አማካይ ቃላት ደግሞ 61.6 ሆኗል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ የስህተት ብዛቱ 2140 ነው። በመቶኛ ሲሰላ 69.4 አማካይ ስህተቱ 42.8 የስህተት ድግግሞሹ 69.4 አንድሁምየትክክለኝነት ተዛማጅነት 1.4 መሆኑ ተረጋግጧል። ይህ ማለት በየ1.4 ቃላት ወይም ሃረጋት ውስጥ ስህተት እንደሚፈጸም ያሳየናል።

ባጠቃላይ በድርሰት አንድ እና ሁለት ከአንድ መቶ ድርሰት 5590 የቃላት ብዛት ሲገኝ አማካይ ቃላት ደግሞ 55.9 ሆኖ ተገኝቷል። የስህተት ብዛታቸውን ስናይ ደግሞ 4590 ሆኗል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 82.2

ነው። አማካይ ስህተቱ 45.9 ፣ የስህተት ድግግሞሹ 82.2 ሲሆን የትክክለኙነት ተዛማጅነት ደግሞ 1.2 መሆኑን ጥናቱ ያሳያል።

### 4.1.2. በድርሰቶች ውስጥ የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች

አጥኚው ከድርሰቶቹ ውስጥ ያሉትን ስህተቶች ለይቶ አቅርቧል። ያቀረባቸውም የስህተት አይነቶች የሆሄያት ግድፈት/ስህተት/፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት፣ የቃላት አጠቃቀም እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች በማለት በቅደም ተከተል አቅርቧቸዋል። ይህንንም እያንዳንዳቸውን የስህተት ብዛት ምን ያህል እንደሆነ፣ በመቶኛ ሲሰላ ፣ አማካይ የስህተት ብዛት፣ አማካይ የስህተት ድግግሞሽ እና በመጨረሻም የትክክለኙነት ተዛማጅነትን ለማቅረብ ተሞክሯል።

ሰንጠረዥ 2 በድርሰቶች ውስጥ የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች (ድርሰት አንድ)

| የስህተት ዓይነት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የትክክለኙነት ተዛማጅነት |
|---|---|---|---|---|---|
| የሆህያት ግድፈት | 810 | 32.2 | 16.2 | 32.2 | 3 |
| የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት | 560 | 22.3 | 11.2 | 22.3 | 4.4 |
| የቃላት አጠቃቀም ስህተት | 55 | 2.1 | 1.1 | 2.1 | 45.6 |
| መለየት ያልተቻሉ | 30 | 1.19 | 0.6 | 1.1 | 83.6 |
| ድምር | 1455 | 57.9 | 29.1 | 5.8 | 1.7 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው ተተኳሪ ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ስህተት በብዛት የታየው የሆህያት ግድፈት ወይም ስህተት ነው። ይሄውም 810 የሚሆን ስህተት ሲታይ በመቶኛ ሲሰላ 32.2 ያህል ያሳያል። አማክይ ስህተቱም 16.2 ሆኖ አግኝተነዋል። የስህተት ድግግሞሽነቱም 32.2 ሲሆን የትክክለኙነት ተዛማጅነቱ ደግሞ 3 ነው። ይህ የሚያመለክተው በከፍተኛ ሁኔታ የሆህያት ስህተት እንደሚፈጸም ጥናቱ ያሳያል።

 በሁለተኛ ድረጃ ስህተት በብዛት የታየው የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነው። የስህተቱም ብዛት 560 ሲሆን በመቶኛ 22.3 ነው። የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀሙ 11.2 አማካይ ስህተት ሲያሳይ የስህተት ድግግሞሽነቱ ደግሞ 22.3 ሆኖ አግኝተነዋል። የትክክለኝነቱ ተዛማጅነቱ 4.4 ሆኗል።

ከዚህ በመቀጠል በስህተት ብዛት ሶስተኛ የሆነው የቃላት አጠቃቀም ስህተት ነው። ቁጥሩም 55 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላም 2.1 ሆኗል። አማካይ ስህተቱ ደግሞ 1.1 ነው። የስህተት ድግግሞሽነቱ ደግሞ 2.1 ሆኖ ሲታይ የትክክለኘት ተዛምጅነቱ ደግሞ 45.6 ሆኖ ቀርቧል።

በመጨረሻም ከስህተቶቹ ውስጥ አነስተኛ ቁጥር የያዘው መለየት ያልተቻሉ ስህተቶ ናቸው። ቁጥሩም 30 ሲሆን በመቶኛ 1.1 ነው። አማክይ ስህተቱ ደግሞ 0.6 ሆኖ ተግኝቷል። የስህተት ድግግሞሽነቱ ደግሞ 1.1 ነው። የትክክለኘት ተዛማጅነቱ ደግሞ 83.6 ነው።

በአጠቃላይ በድርሰት አንድ ውስጥ 1455 ስህተቶች ተፈጽመዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 57.9 ሲሆን አማካይ ስህተቱ ደግሞ 2.9 እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል። የስህተት ድግግሞሽነት 57.9 ሲያሳይ የትክክለኝነት ተዛማጅነት ደግሞ 1.7 ሆኖ ተገኝቷል።

**ሰንጠረዥ 3** ፡ በድርሰቶች ውስጥ የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች (ድርሰት ሁለት)

| የስህተት ዓይነት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የትክክለኝነት ተዛማጅነት |
|---|---|---|---|---|---|
| የሆህያት ግድፈት | 950 | 30.8 | 19 | 30.8 | 2.1 |
| የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት | 400 | 12.9 | 8 | 12.9 | 7.7 |
| የቃላት አጠቃቀም ስህተት | 50 | 1.6 | 1 | 1.6 | 61.6 |
| መለየት ያልተቻሉ | 40 | 1.2 | 0.8 | 1.2 | 77 |
| ድምር | 1440 | 46.7 | 28.8 | 46.7 | 2.1 |

በድረስት ሁለት ያለውን መረጃ ስንመለከትም የሆህያት ስህተት ከፍተኛ ሆኖ አግኝተነዋል የስህተት ብዛቱም 950 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ 30.8 ሲሆን አማካይ ስህተቱ ደግሞ 19 ሆኗል። የስህተት ድግግሞሽነቱ አግሞ 30.8 ነው። የትክክለኝነት ተዛማጅነቱ ደግሞ2.1 መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል።

በሁለተኛ ደረጃ ስህተቱ ከፍ ብሎ የሚታየው የስርዓተ ነጥብ ስህተት ነው። የስህተት ብዛቱም 400 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ 12.9 እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል ማካይ ስህተቱም 8 ሆኖ ፣ የስህተት ድግግሞሽነቱ 12.9 መሆኑን ጥናቱ ሲያሳይ የትክክለኝነት ተዛማጅነቱ ደግሞ 7.7 መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል።

በስህተት ብዛት ሶስተኛ ደረጃ የሆነው የቃላት አጠቃቀም ሲሆን የስህተት ብዛቱም 50 ነው።በመቶኛ ሲሰላም 1.6 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 1 መሆኑን የጥናቱ ትንተና ያሳየናል። የስህተት ድግግሞሽነቱም 1.6 በመሆን የትክክለኝነት ተዛማጅነቱ 61.6 ሆኖ ተገኝቷል።

በመጨረሻ ደረጃ በሰንጠረዡ የታየው መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች የሚለው ነው። የስህተት ብዛቱም 40 ነው። በመቶኛ ሲሰላም 1.2 ሲሆን አማክይ ስህተቱ ደግሞ 0.8 ሆኖ ተመዝግቧል። የስህተት ድግግሞሽነቱም 1.2 ሲሆን የትክክለኝነት ተዛማጅነቱ ደግሞ 77 እንደሆነ ትንተናው ያሳያል።

በአጠቃላይ በድርሰት ሁለት 1440 ስህተቶች ሲገኙ በመቶኛ ሲሰላም 46.7 ነው። አማካይ ስህተቱም 28.8 ሲሆን የስህተት ድግግሞሽነቱ 46.7 መሆኑን ያሳያል። የትክክለኘንት ተዛማጅነቱ ደግሞ 2.1 መሆኑን ጥናቱ አሳይቶናል።

### 4.1.3 **በሆሄያት አጻጻፍ ላይ የታዩ ስህተቶች**

አንድ ጽሁፍ ጥሩ አንባቢ እንዳገኝ ከተፈለገ ሆሄያትን ወይም ፊደላትን በትክክል መጻፍ እና በትክክለኛ ቦታ ላይ መገኘት አለባቸው። አንድ ጸሃፊ በሚጽፈው ጽሁፍ ውስጥ ሆሄያትን በትክክል መጻፍ ካልቻለ መልዕክቱን በትክክል ማስተላለፍ አይችልም። በመሆኑም ጸሃፊው እና አንባቢው መካከል ያለው ግንኙነት ጥሩ የመሆን እድል የለውም። ስለዚህ በጽሁፍ ወቅት ለሆሄያት የሚሰጠው ትኩረት ትልቅ ሊሆን ይገባል።

በዚህ የሀያት ስህተት ውስጥ የሚፈጠረው ችግር እንደየጸሃፊው ይለያያል። ብዙ ጊዜ የሚፈጠረው ፊደላትን መተው ወይም መዝለል፣ ቅርጽን በትክክል አለመጻፍ፣ በሌላ ሆህያት መታካት፣ ሆህያትን መጨመር ወይም መቀነስ ሊሆን ይችላል።

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮችም በተተኳሪ ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ተስተውለዋል።በተለይ የፊደላትን ቅርጽ በትክክል አለመጻፍ ጎልቶ ታይቷል። በመሆኑም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኩረት ሊሰጡት እንደሚገባ ጥናት ያሳያል።

ሰንጠረዥ 4 ፡ በድርሰቶች ውስጥ የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች (ድርሰት ሁለት)

| የስህተት አይነት | የሆህያተጻጻፍ ስህተት |
|---|---|
| የስህተት ብዛት | 810 |
| አማካይ ስህተት | 16.2 |
| ጠቅላላ ስህተት | 1455 |
| በመቶኛ | 57.9 |
| ጠቅላላ ቃላት ብዛት | 2510 |
| አማካይ ቃላት | 50.2 |
| የስህተት ድግግሞሽ | 57.9 |
| የትክክለኝነት ተዛማጅነት | 3 |

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው በተተኳሪ ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ በድርሰት አንድ 810 በድርሰት ሁልት ደግሞ 950 ያህል የሆህያት ስህተት ተስተውለዋል። ይህም ስህተት በድርሰቱ ከተፈጸሙት ስህተቶች ውስጥ ከፍተኛው ሆነው ተገኝተዋል። በመሆኑም የሆህያት ወይም የፊድላት ስህተት ተማሪዎቹ በድርሰት አንድ 57.9 በድርሰት ሁለት ደግሞ 30.8 የስህተት ድግግሞሽ ፈጽመዋል ማለት ነው። ይህም የሆነው በድርሰት አንድ 2510 በድርሰት ሁለት ደግሞ ከ3080 ቃላት ውስጥ ነው።ይህንንም በድርሰት ሁለት የተፈጸሙትን በሚከተለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል።

ሰንጠረዥ 5 በድርሰት ሁለት የሆህያትን አጻጻፍ ስህተት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የስህተት አይነት | የሆሄያት አጻጻፍ ስህተት |
|---|---|
| የስህተት ብዛት | 950 |
| አማክይ ስህተት | 30.8 |
| ጠቅላላ ስህተት | 1440 |
| በመቶኛ | 46.7 |
| ጠቅላላ ቃላት ብዛት | 3080 |
| አማካይ ቃላት | 61.6 |
| የስህተት ድግግሞሽ | 30.8 |
| የትክክለኝነት ተዛማጅነት | 2 |

ከላይ በሰንጠረዥ 4 እና 5 ላይ እንደተመለከትነው ሆሄያት ድምጾችን የሚወክሉ ምልክቶች እንደመሆናቸው መጠን ትኩረት ካልተደረገበቸ አሳሳቢ እንደሆነ ይህ የተማሪዎቹ የስህተት ትንታኔ ያሳያል። ፊደላት ወይም ሆህያት በተገቢው መንገድ ካልተቀመጡ ጸሃፊው ሊያስተላልፍ የፈለገው መልክት እክል ይገጥመዋል። በዚህ ጥናት እንደሚታየው በድርሰት አንድ በየ3 ቃላት ወይም ሃረጋት በድርሰት ሁለት

ደግሞ በየሁለት ቃላት ወይም ሃረጋት ስህተት እንደሚፈጽሙ የትክክለኝነት ተዛማጅነት አሃዞች ይጠቁማሉ፡፡

በድርሰት አንድ

| **ተጽፎ** | **የተገኘው** | |
|---|---|---|
| **መጻፍ** | **የነበረበት** | |
| የማረ | የተማረ | አስተማረ |
| አስተማሪ | | |
| ስራ ቢያጠፋ | ስራ ቢጠፋ | |

በድርሰት ሁለት

| **ተጽፎየተገኘው** | **መጻፍ የነበረበት** |
|---|---|
| ኬቤት | ከቤት |
| ባላዊ | ባህላዊ |
| ይቀቃል | ይንቃቃል |
| ይጣዳ | ይጣዳል |

ከላይ ያሉትን የሆህያት ስህተት ስናይ በቃላት ውስጥ የፊደላት መቀነስ ፣መጨመር ፣ ያለአግባብ መግባት የሆህያትን ቅርጽ በትክክል አለመለየት ተስተዉሏል፡፡

### 4.1.4 **የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች**

ጽህፈት በአግባቡ ትርጉሙ ሳይዛባ ለአንባቢ ለማድረስ ስርዓተ ነጥብ አስፈላጊ ምልክት ነው ፡፡ ይህ ምልክት የራሱ የሆነ የመግቢያ ቦታ እና አገልግሎት አለው፡፡ ስርዓተ ነጥቦች የተለያዩ ቅርጽ እና አገልግሎት ያላቸው ምልክቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ተጠቃሚው የስርዓተ ነጥብ አይነቶችን ምልክቶችን እና አገልግሎቶችን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት፡፡

የተተኳሪ ተማሪዎችም የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ምልክቶችን በአግባቡ አለማወቅ እና አገልግሎቶችቸውንም መዘንጋት ነው ። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ ተተኳር ተማሪዎቹ በድርሰቶቻቸው ውስጥ የፈጸሙትን የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ያሳያል።

ሰንጠረዥ 6 የስርዓተ ነጥብ ስህተትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የስርዓተ ነጥብ አይነት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አጠቃላይ ስህተት | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የትክክለኝነት ተዛማጅነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሁለት ነጥብ | 300 | 53.5 | 560 | 20 | 39.8 | 8.3 |
| አራት ነጥብ | 150 | 26.7 | | 10.3 | 20.5 | 16.7 |
| ነጠላ ሰረዝ | 100 | 17.8 | | 6.8 | 13.5 | 25.1 |
| ጥያቄ ምልክት | 10 | 1.7 | | 0.6 | 1.1 | 251 |
| ድምር | 560 | 38.7 | 1445 | 21 | 57.9 | 1.71 |

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው ከስርዓተ ነጥብ አጠቃላይ ስህተቶች ከ560ው 300 የሚሸፍነው የ ሁለት ነጥብ ስህተት ነው ። ይህ ስህተት በመቶኛ ሲሰላ 53.5 ሲሆን አማካይ ስህተቱ 20 ነው ። ከድርሰት ፈተናው በኋላ በተገኘው ጽሁፍ ውስጥ ሁለት ነጥብን አገልግሎቱን አያውቁም ወይም በቃል እና ቃል መካከል ክፍተት መጠቀም መርጠዋል የሚል ግምት አለ። ይህን ለማለት የተቻለበት ምክንያት ከስርዓተ ነጥቦች በላጩን የወሰደው የሁለት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት በመሆኑ ነው ። የስህተት ድግግሞሽነቱም 39.8 ሲሆን የትክክለኝነት ተዛማጅነቱም 8.3 መሆኑ ጥናቱ አሳይቷል።

በሁለተኛ ደረጃ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ብዛት ያለው ሆኖ የተገኘው አራት ነጥብ ነው። የስህተት ብዛቱም 150 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ 26.7 ነው ። አማካይ ስህተቱም 10.3 ነው። የስህተት ድግግሞሹ 20.5 ሲሆን የትክክለኝነት ተዛማጅነቱም 16.7 ሆኖ ተገኝቷል። በሶስተኛ ደረጃ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት የታየው የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ነው ። ነጠላ ሰረዝ ተመሳሳይነት ያለው ነገሮችን በዝርዝር እና በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ እንደሚያግዝ ይታወቃል ። ተተኳሪ ተማሪዎች ግን ካላስፈላጊ እና ዝርዝር ጉዳይ ያልሆኑ በታዎች ላይ ተጠቅመዋል ። የስህተት ብዛቱም 100 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ 17.8 ነው ። አማካይ ስህተቱም 6.8 እና የስህተት ድግግሞሽነቱም 13.5 ሆኗል። የትክክለኝነት ተዛማጅነቱ ሲታይ ደግሞ 25.1 እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል ።

በመጨረሻ ደረጃ ላይ ከተገኙ ቁጥሮች አነስተኛ የስርዓተ ነጥብ ስህተት የታየበት የጥያቄ ምልክት ነው። ተተኳሪ ተማሪቹ የጥያቄ ምልክትን ጥቅም አውቀው ነው ወይስ የድርሰቱ ጽሁፍ ለጥያቄ ምልክት አላጋለጣቸውም የሚለው ሌላ ጥያቄ ቢሆንም ከአጠቃላይ ስርዓት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ከፈጸሙ ሲታይ ብዙም ስርዓት ነጥብን ጠንቅቀው እንደማያውቁት እንረዳለን ። በአጠቃላይ በድርሰት አንድ 560 የስርዓተ ነጥብ ስህተት የታየ ሲሆን በመቶኛ ሲሰላም 38.7 ነው። ይህም ከአጥቃላይ የስህተት ብዛት ከ1445 መሆኑ ነው። አማካይ ስህተቱም 21.9 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹም 57.9 ሆኖ ተገኝቷል። በአጠቃልይ በድርሰት አንድ የታየው ጥናት የተተኳሪ ተማሪዎችን በየ1.7 ቃላት ወይም ሃረጋት መካከል ስህተት እንደሚፈጽሙ የትክክለኝነት ተዛማጅነት ቁጥሩ ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 7 የስርዓተ ነጥብ ስህተትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የስርዓተ ነጥብ አይነት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ | አጠቃላይ ስህተት | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የትክክለኝነት ተዛማጅነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሁለት ነጥብ | 260 | 65 | 400 | 18 | 29.2 | 11.8 |
| አራት ነጥብ | 90 | 22.5 | | 6.2 | 10.1 | 34.2 |
| ነጠላ ሰረዝ | 43 | 10.7 | | 2.9 | 4.7 | 71.6 |
| ጥያቄ ምልክት | 7 | 1.2 | | 0.4 | 0.6 | 440 |
| ድምር | 400 | 27.7 | 1140 | 46.7 | 28.8 | 2.1 |

በድርሰት ሁለት አጠቃላይ 1440 ስህተቶች ሲፈጸሙ ከነዚህ መካከል 400 የሚሆኑ የስርዓተ ነጥብ ስህተቶች ተገኝተዋል። ከነዚህ ስህተቶች መካከል በከፍተኛ ደረጃ የስህተት ብዛት የታየው የሁለት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነው ብዛቱም 260 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላም 65 ተመዝግበዋል። አማክይ ስህተቱም 18፣ የስህተት ድግግሞሹም 29.2 ሲሆን የትክክለኝነት ተዛማጅነቱም 11.8 እንደሆነ የጥናቱ ትንተና ያሳያል። ይህም ማለት በየ11.8 ቃላት ወይም ሃረጋት መካከል ተተኳሪ ተማሪዎች ስህተት ይፈጽማሉ።

በሁለተኛነት ደረጃ የስርዓተ ነጥብ ስህተት ብዛት የታየው የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነው ። በብዛቱም 90 ያህል ነው ። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 22.5 ይሆናል። አማካይ ስህተቱ 6.2 ሆኖ ተመዝግቧል። የስህተት ድግግሞሽነቱም 10.1 ሆኖ ተገኝቷል ። በ34.2 ሃረጋት እና ቃላት መካከል የተተኳሪ ተማሪዎችን ስህተት እንደሚፈጽሙ የትክክለኝነት ተዛማጅነቱ ቁጥር ያሳየናል ። የሶስተኛ ደረጃን የያዘው የስርዓተ ነጥብ ስህተት የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተት ነው። ቁጥሩም 43 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላም 10.7 እንደሆነት ጥናቱ ይጠቁማል። አማካይ ስህተቱም 2.9 ሆኖ ተመዝግቧል። የስህተት ድግግሞሽነቱም 4.7 ሲያሳይ በየ7.6 ቃላት ወይም ሃረጋት መካከል ተተኳሪ ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ ስህተት እንደሚፈጽሙ የመረጃ ትንተናው ያሳያል ።

የመጨረሻውን ደረጃ የያዘ የርዓተ ነጥብ ስህተት ብዛት የጥያቄ ምልክት አጠቃቀም ስህተት ነው። ይህ ስህተት 7 ብችሃ ሲሆን በመቶኛ ሲሰላም 1.2 ሆኖ ተገኝቷል ።አማካይ ስህተቱም 0.4 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹም 0.6 መሆኑን ጥናቱ ያመልክታል ። በ440 ቃላት ወይም ሃረጋት መካከል የጥያቄ ምልክት ስህተት እንደሚፈጸም የትክክለኝነት ተዛማጅነት መረጃ ያመለክታል። በአጠቃላይ በድርሰት ሁለት በጠቅላላው 1440 ስህተት ሲፈጸም የስርዓተ ነጥብ ስህተት ደግሞ 400 መሆኑን ጥናቱ ያሳያል ይህም በመቶኛ ሲሰላ 27.7 ሆኗል። አማካይ ስህተቱ 46.7 ፣ የስህተት ድግግሞሹ 28.8 እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል። በድርሰት ሁለት በየ2.1 ሃረጋት ወም ቃላት መካከል የስርዓተ ነጥብ ስህተት እንደሚፈጸም የትክክለኝነት ተዛማጅነት ቁጥሩ ያሳያል።

### 4.1.5 **የቃላት አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች**

ቃላት በጽህፈትም ሆነ በንግግር ላይ ለመግባባት መሰረት ናቸው። የመልዕክት ማስተላለፊያ እና መቀበያም ናቸው። በመሆኑም መልዕክቱም ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል በጽህፈትም ሆነ በንግግር ወቅት ያለእንከን ሊገለጹ ይገባል። Raimes (1991:7) እንደሚያስረዱት አንድ ጸሃፊ የቋንቋውን ቃላት በተገቢው ቦታ ካልተጠቀመ ሊተላለፍ የተፈለገው ሃሳብ ተድበስብሶ ሊቀር ይችላል ። ምክንያቱም በማንበብ ሂደት አንባቢው የሚያጋጥመውን ግልጽ ያልሆነ ሃሳብ ከጸሃፊው ጠይቆ ምልሹን ሊያገኝ አይችልም።

ከላይ ምሁሩ እንደገለጹት ጽህፈት ላይ የቃላት አጠቃቀማችን ጥንቃቄን እንደሚያስፈልገው እና ምናልባት ስህተት ቢፈጠር ደግሞ ጸሃፊውን ምን ብለህ ነው የጻፍከው ብሎ ለመጠየቅ ወዳው ምላሽ የማገኘት

እድሉ የለንም። ስለዚህ በጽህፈት ወቅት የታዩ ችግሮችን ለመፍታት ሁላችንም የየድርሻችን ልንወጣ ይገባል።

ሰንጠረዥ 8 በድርሰት አንድ ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ስህተትን የሚያሳይ

| **የስህተት አይነት** | **የቃላት አጠቃቀም ስህተት** |
|---|---|
| የስህተት ብዛት | 55 |
| አማካይ ስህተት | 1.1 |
| ጠቅላላ ስህተት | 1445 |
| በመቶኛ | 57.9 |
| ጠቅላላ ቃላት | 2510 |
| አማካይ ቃላት | 50.2 |
| የስህተት ድግግሞሽ | 2.1 |
| የትክክለኝነት ተዛማጅነት | 45.6 |

ከላይ በሰንጠዡ የተቀመጠው መረጃ እንደሚጠቁመው ባጠቃላይ በድርሰት አንድ ከ1445 ጠቅላላ ስህተት ውስጥ የቃላት አጠቅቀም ስህተት 55 መሆኑ ያሳይል። ይህም ከአተቃላዩ በመቶኛ ሲሰላ 2.1 ሆኖ እናገኘዋለን ጥናቱ በድርሰት አንድ ከተገኙት ጠቅላላ ቃላት 2510 ውስጥ 1.1 በሆነ አሃዝ ተማሪዎቹ ስህተት ይፈጽማሉ። የትክክለኝነት ተዛማጅነት ሲታይ ደግሞ 45.6 በሆነ መልኩ በጽህፈት ውስጥ ስህተት ይፈጽማሉ ማለት ነው።

ሰንጠረዥ 9 ድርሰት ሁለት ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ስህተትን የሚያሳይ

| **የስህተት አይነት** | **የቃላት አጠቃቀም ስህተት** |
|---|---|
| የስህተት ብዛት | 50 |
| አማካይ ስህተት | 1 |
| ጠቅላላ ስህተት | 1440 |
| በመቶኛ | 46።7 |

| | |
|---|---|
| ጠቅላላ ቃላት | 3080 |
| አማካይ ቃላት | 61.6 |
| የስህተት ድግግሞሽ | 30.8 |
| የትክክለኝነት ተዛማጅነት | 61.6 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው በድርሰት ሁለት ካጠቃላይ 3080 ቃላት ውስት 50 የሚሆኑ ቃላት ስህተት ሆነው ተገኝተዋል ይህም የሆነው ከአጠቃላዩ የስህተት ብዛት 1440 መካከል ነው ። በመቶኛ ሲሰላ 46.7 ሆኖ ተመዝግቧል። የስህተት ድግግሞሹም 30.8 ሲሆን ተጠኚ ተምሪዎቹ በየ61.6 ቃላት ወይም ሃረጋት መካከል የቃላት አጠቃቀም ስህተት እንደሚፈጽሙ ትንተናው ያመላክታል ። ተማሪዎቹ ከፈጸሙት ስህተቶች መካከል ለምሳሌ ለማቅረብ ያህል

ከድርሰት አንድ

| **ተጽፎ የተገኘ** | **መጻፍ የነበረበት** |
|---|---|
| ቡንማር | ብንማር |
| ባንክብት | ባንክ ቤት |
| ሃክም | ሀኪም |
| ኤኔ | እኔ |
| ዥምር | ጀመረ |

ከድርሰት ሁለት

| **ተጽፎ የተገኘ** | **መጻፍ የነበረበት** |
|---|---|

| | |
|---|---|
| ያሬጋል | ያረጋል |
| በዋላ | በኃላ |
| መስበላ | በሶ ቢላ |
| ምንምጣ | ሚጥሚጣ |
| ጠርጠን | ጠርተን |

ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች በድርሰት አንድ እና ሁለት ተተኳሪ ተማሪዎቹ ከፈጸሙት ስህተቶች ለምሳሌ ያህል ለማሳየት እንጅ እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ አጥኚው ለማረጋገጥ ይፈልጋል።ከዚህ ውጭ በአጥኚው መለየት ወይም መገመት ያልተቻሉ ቃላት መኖራቸውን ለመግለጽ ይወዳል።

### 4.1.6 **መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች**

በጥናቱ ውስጥ ዝቅተኛ ደረጃውን የያዘው የስህተት ዓይነት መለየት ያልተቻሉ ወይም ለማንበብ አልያም ለማስተካከል እና ለመገመት የከበዱ ቃላቶች በተተኳሪ ተማሪዎች የተጻፉ ቃላቶች ተገኝተዋል። በድርሰት አንድ ከ1445 ስህተቶች መካከል 30 የሚሆኑ ቃላት መለየት ያልተቻሉ ናቸው። እነዚህም ስህተቶች ከአጠቃላይ ስህተት በመኦትኛ ሲሰሉ 1.1 ሆኗው ተመዝግበዋል ። በድርሰት ሁለት ደግሞ 1440 ስህተት መካከል መለየት ያልተቻሉ ተብለው የተፈረጁት 40 የሚሆኑ ቃላት ናቸው ይህም በመቶኛ ሲሰላ 1.2 ሆኖ ተመዝግቧል። የትክክለኛነት ተዛማጅነት ስናይ በድርሰት አንድ 83.6 ቃላት ወይም ሃረጋት በድርሰት ሁለት ደግሞ 77 ነጥብ በሆነ አሃዝ ተማሪዎቹ ስህተት ይፈጽማሉ። ይህ ሲታይ ከተጠቀሱት ስህተቶች አንጻር ዝቅተኛ የስህተት አይነት የተፈጸመው ወይም የተመደበው በዚህ ክፍል ነው። **ለምሳሌ ያህል ፦**

**ከድርሰት አንድ**

የትማራ፣አረኛ

የማራ ፣ ቁንፋቴና የተቃማ የሚሉት ናችው ።

ከድርሰት ሁለት

በባር፣ ኤጣታና፣ ኬረቶና ጉበይ

እነዚህ ምሳሌዎች ብዙ ምሁራን ጽህፈት ከባድ የሆነ እና ጥንቃቄ የሚጠይቅ እንደሆነ ለምን እንደገለጹ ትልቅ ማስረጃ ነው።ምክንያቱም አንባቢ እና ጸሃፊ በአንድ ላይ ወይም ፊት ለፊት የማይገናኙበት የቋንቋ ክሂል በመሆኑ ምን ለማስተላለፍ እንደፈለገ አንባቢው ሳይረዳ የሚቀር ይሆናል።ለዚህም ከላይ የተዘረዘሩት ጥሩ ማሳያ ናቸዉ ማለት ይቻላል።

# 1. 4.2 ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት የመጀመሪያው የመረጃ መሰብሰቢያ የድርሰት ፈተና እንደሆነና አጥኚውም ያሉትን መረጃዎች ከላይ ለማቅረብ ሞክሯል ። በሁለተኛ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ደግሞ ለተተኳሪ ተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ነው ። በጽሁፍ መጠይቁ 20 ወንዶች እና 30 ሴቶች በድምሩ 50 ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን ያለውን የጥናት ዉጤትም እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 4.2.1 **ከዝግ የጽሁፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና**

ይህ የጽሁፍ መጠይቅ በድርሰት ውስጥ ለሚፈጸሙ ስህተቶች መንስኤው ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል። ለዚህም ሰባት ዝግ እና 3 ክፍት ጥያቄዎች ለተማሪዎቹ ቀርቦ መረጃ ተሰብስቧል። የመረጃውም ዉጤት ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 10 የአማርኛ መምህራን ድርሰት የማጻፍ ሁኔታን የሚያሳይ ትንታኔ

| ተ.ቁ | የጥያቄው አይነት | አማራጭ | ምላሽ የስጡ ተማሪዎች | በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ድርሰት እንደትጽፉ የአማርኛ መምህራችሁ ያዛችኋል? | አንዳንድ ጊዜ | 30 | 60 |
| | | ሁልጊዜ | 6 | 12 |
| | | ብዙ ጊዜ | 8 | 16 |
| | | ተሰጥቶ አያውቅም | 6 | 12 |
| ድምር | | | 50 | |

ከላይ በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው ድርሰት እንድጽፉ የአማርኛ መምህራችሁ ያዛችኋል? ለሚለው ጥያቄ ተተኳሪ ተማሪዎቹ 30 የሚሆኑት አንዳንድ ጊዜ እንደሚታዘዙ መረጃ ሰተዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ ወደ 60 ደርሷል ። መረጃው እንደሚያሳየውም የጽሁፍ መልመጃ ይሆን ዘንድ የአማርኛ መምህራን እንድጹ ያዟቸዋል ። ሆኖም ለድርሰቱ ወይም በፈተናው ዉጤት ያላመጡት የአተገባበር ሁኔታ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታመናል። 8 የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ብዙ ጊዜ የጽሁፍ መልመጃ እንደሚሰጣቸው ምልሽ ሰጥተዋል። በመቶኛ ሲሰላም 16 ይሆናል። ይህ ምላሽ ጥሩ ቢሆንም የድርሰቱ ፈተና ላይ ግን የተገኘው መረጃ ልምምድ የሚያደርጉ አያስመስላቸውም። 6 የሚሆኑ ተተኳሪ ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ የድርሰት ጽሁፍ እንድጽፉ እንታዘዛለን ብለዋል። ይህ ምላሽ እውነትነት ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም። ምክንያቱም ሁልጊዜ የድርሰት ጽሁፍ ልምምድ አያደርጉም እና ወይም ያለጥንቃቄ መልስ የሰጡ ያስመስላቸዋል። ሌላው 6 የሚሆኑ ተተኳሪ ተማሪዎች ደግም ጭራሽ የጽሁፍ መልመጃ ተሰጥቶን አያውቅም በማለት መልስ ሰጥተዋል ። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 12 ሆኗል።

በአጠቃላይ በጥያቄ አንድ መምህራችሁ የጽሁፍ ድርሰት እንድጽፉ ያዟችኋል በሚለው ጥያቄ የአኣብዛኛው መልስ አንዳንድ ጊዜ ይሰጠናል የሚል ነው። ይህም መምህራን ለተማሪዎቻችን ድርሰት መጻፍ እንዲለማመዱ የማያደርጉ ከሆነ ለተማሪዎቹ የድርሰት መጻፍ እድገት ሊያመጣ እንደማይችል ጥናቱ ያሳያል።

ሰንጠረዥ 11 የድርሰት ጽሁፍ የቤት ስራ መስጠትን የሚያሳይ ትንታኔ

| ተ.ቁ | የጥያቄው አይነት | አማራጭ | ምላሽ የስጡ ተማሪዎች | በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|---|
| 2 | የጽሁፍ የቤት ስራ ይሰጣችኋል? | አንዳንድ ጊዜ | 30 | 64 |
| | | ሁልጊዜ | 8 | 11.6 |
| | | ብዙ ጊዜ | 6 | 12 |
| | | ተሰጥቶ አያውቅም | 4 | 8 |
| ድምር | | | 50 | |

ከላይ ከሰንጠዡ እንደምንረዳው 30 የሚሆኑ ወይም 64 በመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች የጽሁፍ የቤት ስራ አንዳንድ ጊዜ ይሰጠናል የሚል ምልስ በጽሁፍ መጠይቃቸው መረጃ ሰተዋል ። ይህም ጥሩ ጎን እንዳለው ይገመታል ምክንያቱም ተማሪዎች በክፍ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከመምህራቸው ርዕስ ይዞ በመሄድ የቤት ስራ ሰርተው የተሻለ ይሆናል። 8 ይሚሆኑ ተማሪዎች ወይም 16 በመቶ የሚሆኑት የጽሁፍ የቤት ስራ ሁልጊዜ ይሰጠናል ብለዋል። ይህ የድርሰት ጽሁፍን ልምምድ ብቻ ከግምት ያስገቡ ነው ተብሎ አይገመትም። ሁልጊዜ የድርሰት ጽሁፍ የቤት ስራ የሚሰጥ መምህር አይኖርም። ምክንያቱም ሌሎች የቋንቋ ክሂልን የሚያስተምርበት እና የቤት ስራ የሚሰጥበት ጊዜ ሰማይኖር ነው ።

በሶስተኛ ደረጃ የተማሪ ብዛት ያለው ብዙጊዜ የጽሁፍ የቤት ስራ እንሰጣለን የሚለው ነው።ብዛታቸው 6 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላም 12 በመቶ ሆኗል። ሌላው ዝቅተኛ የተማሪ ቁጥር የተገኘበት የጽሁፍ የቤት ስራ ተሰጥቶ አያውቅም የሚለው ነው። ብዛቱም 4 ብቻ ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ ደግሞ 8 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል።

ሰንጠረዥ 12 መምህራን የድርሰት ጽሁፍ የቤት ስራን የመከታተል ሁኔታን የሚያሳይ ትንታኔ

| ተ.ቁ | የጥያቄው አይነት | አማራጭ | ምላሽ የስጡ ተማሪዎች | በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|---|
| 3 | የጻፋችሁትን የቤት ስራ መምህራችሁ ያርማሉ? | አንዳንድ ጊዜ | 36 | 72 |
| | | ሁልጊዜ | 10 | 20 |
| | | ብዙ ጊዜ | 3 | 6 |
| | | አይታረምም | 1 | 2 |
| ድምር | | | 50 | |

የመምህራን የድርሰት ጽሁፍ የቤት ስራ መሰጠት እና ክትትልን የሚያሳየው 36 የሚሆኑ ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚታረም በጽሁፍ መጠይቃቸው ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 72 ይደርሳል። 10 የሚሆኑት ደግሞ ሁልጊዜ የቤት ስራ ይታረማል ብለው ምላሽ ሰጥተዋልይህ መረጃ እውነት ከሆነ የሚበረታታ ነው። የድርሰት ጽሁፍ የቤት ስራችን ብዙ ጊዜ ይታረማል ያሉት ደግሞ 3 ተማሪዎች ናቸው። በመቶኛ ሲሰላ ደግሞ 6 በመቶ ሆነ ተመዝግቧል። ዝቅተኛ የተማሪ ቁጥር መላሽ የሰጠበት ደግሞ

የቤት ስራችን ጭራሽ አይታረምም የሚለው ነው። ይህም 1 ተማሪ ብቻ ነው። በመቶኛ ሲሰላም 2 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል።

ሰንጠረዥ 13 በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት የመጻፍ ፍልጎትን በተመለከተ የሚያሳይ ትንታኔ

| ተ.ቁ | የጥያቄው አይነት | አማራጭ | ምላሽ የስጡ ተማሪዎች | በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|---|
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ለመጻፍ ያልህ/ሽ ፍላጎት ምን ያህል ነው? | ከፍተኛ | 15 | 30 |
| | | መካከልኛ | 30 | 60 |
| | | ዝቅተኛ | 4 | 8 |
| | | ምንም ፍላጎት የለኝም | 1 | 2 |
| ድምር | | | 50 | |

ከላይ በሰንጠረዥ ያሉት መረጃዎች የሚያሳዩን 30 የሚሆኑት ተማሪዎች ፍላጎታቸው መካከለኝ እንደሆነ ገልጸዋል ይህም በመቶኛ ሲሰላ 60 በመቶ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ብዙ ተማሪዎች የመለሱት የአማርኛ ድርሰት ፍላጎት ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸዋል። ብዛቱም 15 ተማሪዎች ናቸው። በመቶኛ ሲሰላም 30 በመቶ ነው። በጽህፈት ብቻ ሳይሆን በሌላ የስራ መስክም ፍላጎት ካለ ዉጤቱ ያማረ እንደሚሆን ይታወቃል። በመሆኑም ይህ ለተተኳሪ ተማሪዎች ጥሩ ተስፋ ሰጪ ነው። ሆኖም ግን የሰዎች ፍላጎት ይለያያል እና 4 የሚሆኑ ተማሪዎች ወይም 8 በመቶ የሚሆኑት የድርሰት የመጻፍ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን በጽሁፍ መጠይቅ ምላሻቸው ጠቁመዋል። 2 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ምንም አይነት የአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ለመጻፍ ፍላጎት እንደለላቸው ገልጸዋል። የተማሪዎቻችን የድርሰት ፍላጎት ለመክፈት የሁላችንም ድርሻ የሚጠይቅ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 14 በተማሪው መጽሃፍ ውስጥ ያለውን መልመጃ መስራትን በተመለከተ የሚያሳይ ትንታኔ

| ተ.ቁ | የጥያቄው አይነት | አማራጭ | ምላሽ የስጡ ተማሪዎች | በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|---|
| 5 | በአማርኛ ቋንቋ | አልፎ አልፎ | 24 | 48 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ያለውን የጽሁፍ መልመጃ ትሰራላችሁ? | ሁሉንም | 16 | 30 |
| | | አንሰራም | 7 | 14 |
| | | እርግጠኛ አይደለሁም | 3 | 6 |
| ድምር | | | 50 | |

በድርሰት ጽሁፍ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት በተማሪ መጽሃፍ ውስጥ ያሉትን መልመጃዎች መስራት እና ማሰራት እንድሁም ክትትል ማድረግ ግድ ይላል። ከላይ በሰንጠረዡ የምናየው የተኳሪ ተማሪዎች የጥናት መረጃ እንደሚያሳየን 16 የሚሆኑ ተማሪዎች ሁሉንም መልመጅዎች እንደሚሰሩ ገልጸዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 30 በመቶ ይሆናል። 24 የሚሆኑ ተማሪዎች ማለትም ከፍተኛ የሚሆነው የተተኳሪ ተማሪዎች መልስ የሚያመለክተው ሁሉም የመጽሃፉንመልመጃ ሳይሆን አልፍ አልፎ እንደሚሰሩ ነው። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 48 በመቶ የሚሆኑት ናቸው ። ይህ ጥናት የሚያመለክተው መልመጃዎችን ሳናሰራቸው የምናልፍ ከሆነ ወይም ልምምድ የማናደርግ ከሆነ ለተማሪዎቹ የድርሰት ጽሁፍ መሻሻል ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል። በመሆኑም በመጽሃፉ ያለውን የድርሰት መለማመጃ እንድለማመዱ በማድረግ ለተተኳሪ ተማሪዎች የድርሰት ጽሁፍ ለውጥ ጥረት ሊደረግ ይገባል። ሌላው የተማሪዎች መረጃ የሚያሳየን ምንም የጽሁፍ መልመጃ እንደማይሰሩ ነው። በቁጥር 7 የሚሆኑት ተተኳሪ ተማሪዎች የገለጹት ይህም 14 በመቶ የሚሆኑት ማለት ነው። 3 የሚሆኑ ወይም 6 በመቶ ደግሞ መልመጃ መስራት እና አለመስራታቸን እርግጠኛ አይደሉም ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎች የመጽሃፉን ይዘት ጠንቅቀው አለማወቃቸው ነው።

ሰንጠረዥ 15 የአማርኛ መምህሩ ከተማሪው መጽሃፍ ውጭ ማስተማር አለማስተማሩን የሚያሳይ ትንታኔ

| ተ.ቁ | የጥያቄው አይነት | አማራጭ | ምላሽ የስጡ ተማሪዎች | በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|---|
| 6 | የአማርኛ መምህራችሁ ከመማሪያ | ብዙ ጊዜ | 20 | 40 |
| | | አንዳንድ ጊዜ | 22 | 44 |
| | | አያስተምሩንም | 5 | 10 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | መጽሃፍ ውጭ ያስተምሯችኋል? | እርግጠኛ አይደለሁም | 3 | 6 |
| ድምር | | | 50 | |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከትነው 22 የሚሆኑት ወይም 44 በመቶ ተተኳሪ ተማሪዎች የአማርኛ መምህራቸው ከመማሪያ መጽሃፍ ውጭ አንዳንድ ጊዜ እንደሚያስተምሯቸው ሲገልጹ 20 የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ ከመጽሃፍ ዉጭ ያስተምሩናል ብለዋል፡፡ይህም በመቶኛ ሲሰላ 40 በመቶ ነው፡፡ 5 ተማሪዎች ደግሞ ከመጽሃፍ ውጭ አያተምሩንም ብለዋል ይህም 10 በመቶ የሚሆኑት ማለት ነው፡፡ ሌሎች 3 ተማሪዎች ወይም 6 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከመጽሃፍ ዉጭ መማርን እና አለመማራቸውን እርግጠኛ አይደሉም፡፡ ይህም የተማሪውን የትኩረት ማነስ ሊያመለክት ይችላል ፡፡

ሰንጠረዥ 16 በአማርኛ ድርሰት መጻፍ የመፍራት እና ያለመፍራት ጉዳይ በተመለከተ የሚያሳይ ትንታኔ

| ተ.ቁ | የጥያቄው አይነት | አማራጭ | ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች | በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|---|
| 7 | በአማርኛ ድርሰት መጻፍ ይከብድሃል/ሻል? | በጣም | 10 | 20 |
| | | ብዙም አይከብደኝም | 25 | 50 |
| | | ቀላል ነው | 7 | 14 |
| | | አንዳንድ ጊዜ | 8 | 16 |
| ድምር | | | 50 | |

ከላይ ያለው ሰንጠረዥ እንደሚያሳየን 25 ተማሪዎች ወይም 50 በመቶ የሚሆኑት በአማርኛ ድርሰት መጻፍ ብዙም እንደማይከብዳቸው ገልጸዋል ። 10 ተማሪዎች ደግሞ በጣም ይከብደኛል ብለዋል ይህም 20 በመቶ መሆኑ ነው ። 8 ተማሪዎች ማለትም 16 በመቶ የሚሆኑት አንዳንድ ጊዜ እንደሚከብዳቸው ገልጸዋል ። 7 ወይም 14 በመቶ የሚሆኑት በአማርኛ ድርሰት መጻፍ እንደሚቀልቸው ከሰጡት መረጃ መረዳት ይቻላል።

## 4.2.2 **ከክፍት የጽሁፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች**

በተራ ቁጥር 8 በአማርኛ ድርሰት ለመጻፍ የሚያስቸግሩ ሁኔታዎች ምንምን ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ተተኳሪ ተማሪዎች የተላያየ መልስ ሰጥተዋል ። እንዚህም የሚከተሉ ናቸው።

- ✓ በተልያዩ ችግሮች ምክንያት ክፍለ ጊዜውን ጠብቆ ያለመማር
- ✓ መጽሃፍ ላይ ያለውን ንባብ ለተማሪው አለመነበብ እንዳነቡም ግፊት አለማድረግ
- ✓ ፍርሃት
- ✓ ሃሳብ የማፍለቅ ችግር
- ✓ ቃላትን አዋቅሮ ለመጻፍ አለመሞከር አይም አለመለማመድ የሚሉት ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ ለድርሰት ጽሁፍ የሚሰጡ ርዕሶችን ያለመረዳት ወይም ያለማወቅ እና በትክክል ሆሄያትን ማገጣተም እና የቃላት ምስረታ ጭምር እንደሚከብዳቸው ከጥናቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

በተራ ቁጥር 9 በአማርኛ ድርስት ለመጻፍ ወይም ለማሻሻል ምን ይደረግ ትላለህ/ ሽ? ለሚለው ጥያቄ ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሰጥተዋል። እንሱም

- ❖ የምንጽፈውን ወይም የምንለማመደውን የድርሰት ጽሁፍ መልመጃ ክትትል ቢደረግ
- ❖ የድርሰት ጽሁፍ ፍላጎታችን እንድከፈት ቀለል ያሉ ርዕሶን በመስጠት ብንለማመድ
- ❖ የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሃፍ ጭግር ቢቀረፍ
- ❖ ልዩ የሆነ ድጋፍ እና ክትትል ቢደረግልን
- ❖ መምህራን ክፍለጊዚያቸውን ጠብቀው ቢገቡ እና የጽሁፍ መልመጃዎች ባይዘለሉ
- ❖ መጽሃፍ ላይ ያሉ የድርሰት ሞደሎች ቢነበቡልን፣ ብናነብ አይም እንድንለማመድ ቢደረግ የድርሰት ጽሁፍ ፍላጎታችን ሊሻሻል ይችላል።

- ❖ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ በአማርኛ ቋንቋ መምህር ብንማር የሚሉት ናቸው ። ሌላው በጽሁፋቸው ወይም በምላሻቸው ምን ለማለ እንደፈለጉ የማይታወቅ እና ሃስባቸውን በጽሁፍ መግለጽ ያቃታቸው መኖራቸውን በጥናቱ ታይቷል።

በመጨረሻው ጥያቄ ማለትም በተራ ቁጥር 10 ድርሰት ስትጽፍ/ፊ የሚፈጠረው ስህተት ምክያት ምን ይመስልሃል/ሻል ለሚለው ጥያቄ ተተኳሪ ተማሪዎቹ የሰጡት መልስ የሚከተሉት ናቸው ።

- ➢ ብዙ ንባብ ስለማናነብ የድርሰት ጽሁፍ ለመጻፍ አንችልም
- ➢ መምህራን የማንችለውን ቃል ከአንድበታቸው ያውጣሉ
- ➢ ፍርሃት
- ➢ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን አለመማር
- ➢ የምንማረውን ነገር በግልጽ አለምስማት ወይም ያለመረዳት የሚሉት እና መለየት ያልተቻሉ ብዙ ቃላት በጽሁ መጠይቁ ምላሽ ላይ ተገኝተዋል።

## 4.3 **ከአማርኛ መምህራን ቃለ ምልልስ የተገኙ መረጃዎች**

የዚህ ጥናት የመጭረሻው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር የተደረጉ ቃለ ምልልሶች ናቸው። ቃለ ምልልሱ የተደረገው በማጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ በሰሙይ ትምህርት ቤት የሚሰሩ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት በድምሩ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ነው። ሙሉ መረጃውም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 17 መረጃ የሰጡ መምህራንን የሚያሳይ ትንታኔ

| ተ.ቁ | የመምህሩ ስም | ጾታ | እድሜ | የአገልግሎት ዘመን | የትምህርት ደረጃ | የተመረቁበት እና የሚሰሩበት የትምህርት ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መ/ር አረጋ ደጀን | ወ | 35 | 13 | ድግሪ | አማርኛ |
| 2 | መ/ርት ሮዛ የሱፍ | ሴ | 30 | 10 | ድግሪ | አማርኛ |

ከላይ የተጠቀሱት መምህራን በትምህርት ቤቱ ሲሰሩ የቆዩ በመሆኑ የተተኳሪ ተማሪዎችን ከግምት ያስገባ ሃሳባቸውን ለመስጠት ችለዋል የሰጡትም ሃሳብ በመጠይቁ መሰረት እንደሚከተለው ቀርቧል።

በጥያቄ አንድ ላይ የቀረበላቸው ጥያቄ በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በጽህፈት ወቅት የሚፈጽሙት ስህተት ምንምን ናቸው የሚል ሲሆን መምህራኑም በሚከተለው መልኩ መልስ ሰጥተዋል ። መልሱም በዝርዝር እንደሚከተለው በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በጽህፈት ወቅት የሚፈጽሙት ስህተቶች ብለው ያነሷቸው የሚከተሉትን ነው።

1. የሆሄያት ቅርፅ በትክክል ያለመፃፍ

ይህ ችግር አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ የተማሩትንም ሆነ ያልተማሩትንም ተማርዎች የሚያጠቃልል ነዉ አማርኛን ኢ-አፍ ፈት የሆኑት ላይ ጎልቶ ይታይ እንጅ። በተለይ ሳድስ እና ሳልስ ላይ ችግሩ ጎልቶ ይታያል። የፊደላትን ቅርፅ በትክክል የማይፅፉ ተማርዎች ደግሞ ፅህፈት ምን ያህል እንደሚከብድ ይታወቃል።

የፊደላትን ቅርፅ መለየት 1ኛ-4ኛ ክፍል ባለዉ የክፍል ደረጃ የነበረበት ቢሆንም ጥናቱ ትኩረት ያደረገበትን የ7ኛ ክፍል ተማርዎችንም ማጠቃለሉ ይህ የፊደላትን ቅርፅ ያለመለየት ችግር ምን ያህል ጥናቱ በሚደረግበት አካባቢ የአማርኛ ትምህርት ላይ ያለዉ የአፈፃፀም ወይም የመማር ማስተማር ችግር ዉስብስብ መሆኑን ይጠቁማል በማለት ቃለምልልስ ያደረጉት መምህራን ተናግረዋል።

2. የሆሄያት ስያሜዎችን በትክክል ያለመጥራት

በቃለምልልሱ ወቅት መረጃ የሰጡኝ መምህራን እንደገለፁት ተማሪዎች የፊደላትን ቅርፅ ከተሰጣቸዉ የድምፅ ዉክልና ዉጭ እና የማይገናኝ ወይም የአንዱን ድምፅ ለአንዱ በማድረግ ስሳሳቱ ይታያሉ። ይህም ችግር በሰባተኛ ክፍል የትምህርት ደረጃ መገኘቱ ችግሩ በፅሁፍ ዉስጥ ከምሰጠዉ ቦታ አንፃር የጎላ ክፍተት እንደሆነ መምህራን ይገልፃሉ።

የፊደላትን ቅርጽ ከተሰጣቸው ስያሜ ጋር ያለመጣጣም አይነት ችግር ተይዞ ደግሞ የፅህፈት ስራን የተዋጣ ማድረግ የማይታሰብ መሆኑንን ሳይታለም የተፈታ ነዉ ። ይህ ስህተት ወይም ችግር ደግሞ በ7ኛ ክፍል ደረጃ እልባት መስጠት ይቻላል ለማለት ይከብዳል የሚሉት ጥናቱ ያተኮረባቸዉ መምህራን ይህን ችግር 1ኛ--4ኛ ክፍል ባለዉ የክፍል ደረጃ መፈታት ያለበት ነዉ ብለዋል። በመሆኑም ይህ ችግር የአማርኛ መምህራን ብቻ የሚፈቱት እንዳልሆነ ይታወቅ ብለዋል።

ምክንያቱም ይህን ችግር እንዲከሰትና ለመፍታት ውስብስብ ያደረገው ሌሎች ዘርፈ ብዙ ችግሮች አሉ ብለዋል እነዚህን ችግሮች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

1ኛ የማህበረሰቡ ልጆች ያሉበት ደካማ ኢኮኖሚ መሰረታዊ ፍላጎት የሚያሟላ ባለመሆኑ ለትምህርት ሙሉ ልባቸውን እንዳይሰጡ አደርጓቸዋል፡፡

ይህም ለአማርኛ ትምህርት ብቻ ሳይሆን የራሳቸው የሆነውንም የማጃግ ቋንቋ ጽህፈት እንዳይችሉ አደርጓቸዋል፡፡

2ኛ ሌላው የአማርኛ ፊደል ቅርጽና ስያሜ በተገቢው እንዳያውቁ ያደረጋቸው የተማርዎቹ መዋያና የማህበራዊ ኑሮ መስተጋበራቸው ለትምህርት የሚገፋፋ ባለመሆኑ እንደሆነ መምህራን ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ግን የተማሪዎች የጽሁፍ ክህሎታቸው እንዲያድግ ዛሬም ቢሆን ለማሻሻል የተቻላቸው እያደረጉ  እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

አጥኝውም ወደ ትምርህት ቤቱ ለጥናቱ በተንቀሳቀሰበት ወቅት ተማሪዎች በተደጋጋሚ ከግቢ ውጬ ሰዓት በማሳለፍ ወዲያ ወዲህ ስሉ የተመለከተ ሲሆን ይህንንም ለመምህራን በውይይት ወቅት በማንሳት አስተዋጽኦ ይኖረው ይሆን እንዴ? የሚል ሀሳብ አንስቶ ምላሽ አግኝቷል፡፡ መምህራን ሲመልሱ ለተማሪዎች የጽፈት ክህል ችግር ዘርፈ ብዙ እነደሆነ ገልጸው ሰዓት ማሳለፍ ብቻውን አንድ ምክንያት ይሁን እንጂ የተመሪውን የጽሁፍ ክህሎት ሊያባብሱ የሚችሉ መንስኤዎች ብዙ ናቸው ብለዋል፡፡

ለምሳሌ አንድ ተማሪ በወላጅ እገዛ ቁርስ በልቶ አልባሳት ተሟልቶለት ወደ ትምህርተ ቤት እንዲሄድ ካልተደረገለት ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት ይቀንሳል ፡፡ በተለይ የሁለተኛ መንፈቅ የትምህርት ጊዜያት በማህረሰቡ የምግብ ችግር ወይም እጥረት ስለሚፈጠር ተማሪ ቁርስ ሳይበላ ይመጣል ወይም ሰዓት አሳልፎ ይገባል፡፡

አንዳንድ ጊዜም ያቋርጣል፡፡ ለዚህም ነው የተማሪዎቹ የጽህፈት ክህሎት ችግር ዘረፈ ብዙ ነው የሚባለው ብለዋል፡፡

3. የሥረዓተ- ነጥብ አጠቃቀም ስህተት፡-

ሥረዓተ-ነጥብ ማለት በጽሁፋችን ውስጥ የዓረፍ-ነገራችንን ትርጉም እነዳይዛባ የሚረዳን ምልክት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቻችን የስረዓተ ነጥቦችን ስያሜ መለየትና አገልግሎታቸውንም እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡ይህ ችግርም አጥኝውም ለጥናት ባቀረበው ፈተና ላይ ስህተቶቹ ጎልተው አይቷቸዋል፡፡

አብዛኞቹ ተማሪዎች ምልክቶቹን ያውቋቸዋል፡፡ ሆኖም ግን የእያንዳዱን ስረአተ ነጥብ ምልክት ስያሜን ሲሳሳቱ ይታያል፡፡ አገልግሎቱንም ቢሆን ባልተፈለገ ቦታ ላይ ሲጠቀሙ ታይተዋል፡፡

4. የሀሳብ ማፍለቅ ችግር ፡- የተማሪዎች የጽህፈት ክህል ችግር ላይ ከሚታዩት መካከል አንዱ የሀሳብ ማፍለቅ ችግር ነው፡፡ ይችግር ከመፍራት እና የአማርኛን ትምህርት የጽሁፍ ክህሎት አክብዶ ከማየት የመጣ እንደሆነ መምህራን ተናግረዋል፡፡ ሀሳብ ሲያፈልቁ በውስጣቸው ያለውን ሀሳብ ወረቀት ላይ ማስቀመጥ ከሆሂያት ቅርፅ እና የድምጽ ውክልና ችግር ጋር ተዳምሮ የማይቻል አደርገው እንደሚያስቡት መምህራን ገልጸዋል፡፡

በተግባር ጽሁፍ ፈተናው ላይም ይሄው ችግር ነው፡፡ ተማሪዎች ትንሽ ከጻፉ በኃላ እስክቢርቶን አፍ ላይ በማድረግ ፈተናው እስከሚሰበሰብ ድረስ ይቀመጣሉ፡፡

ይህም የሚሆነው የአማርኛ ትምህርት ከመፍራት የተነሳ እንደሆነ መምህራን ገልጸዋል፡፡

5.የአማርኛ ሰዋሰው ህግጋትን ያለመጠበቅ፡-

አማርኛ የሰዋሰው ህግጋትን ለመጠበቅ ችግር በተማሪዎች ፈተና ጊዜ የታየ ቢሆንም

ቃለምልልስ ያደረጉት መምህራንም በንግግራቸው ወቅት ይህንኑ ችግር አንስተውታል፡፡ በዓረፍተ-ነገር መጀመርያ ምን ይመጣል ቀጥለውስ በዓረፍተ-ነገር መጨረሻ ለይስ ምን ይሁን የሚመጣው ባለቤት ነው ወይስ ተሳቢ መግባት ያለበት ግስ በየት ቦታ ነው የሚገባው የሚለውን የማይለዩ ተመሪዎች ብዙ መሆናቸውን መምህራን ገልጸዋል፡፡

ጽህፈት ክህል ደግሞ ህግ መጠበቅ በጣም አስፈላጊ እና ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል ምክንያቱም የቋንቋውን ህግጋት ጠብቀን ካልጻፍን ለተደራሲያን ለማስተላለፍ የተፈለገው መልዕክት በትክክል የመድርስ እድሉ አንስተኛ እንደሆነ የቃለምልልስ ተሳታፊዎቹ አረጋግጠዋል፡፡

6. የአማርኛ ድርሰት ለመጻፍ ያለው ፍላጎት መቀነስ

መምህራን በቃለምልልስ ወቅት እነደገለጹልኝ ይህ የድርሰት ጽሁፍ ፍላጎት መቀነስ የታየው ከላይ የተጠቀሱ ችግሮች በተማሪው ላይ በመገኘታቸው የመጣ ድምር ችግር ነው፡፡ መምህሩ ስያብራሩ በድርሰት

ጽሁፍ ውስጥ ተማሪዎች ችግር ስያጋጥማቸው እና ስተቶቹ የጎሉ ስመጡ ተማሪው ተስፋ የቆረጠ የመምጣት ምልክት ይታያል።

አጥኝውም ከላይ የተጠቀሱ ችግሮች በሙሉ እውነት ያላቸው በመሆኑ መምህራንም ሆኑ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በትብብር በመስራት ችግሮችን በሙሉ ማጥፋት ባይቻል እንኳን መቀነስ እንደምቻል ያምናል። ስለዚህም ሁላችንም ልንተግብር ይገባል።

ጥያቄ 2. ተተኳሪ ተማሪዎቹ የስህተት ምንጫቸው ምን ይሆናል ብለው ይገምታሉ? በማለት ለሁለቱም መምህራን ተራ በተራ ጥያቄ ባቀረብኩበት ወቅት የሚከተለውን መልስ ሰጥተውኛል።

መ/ር 1 የስህተት ምንጭ የሚሆኑ ብዙ ነገሮች ቢሆኑም የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያክል

- ለትምህርቱ ትኩረት አለማድረግ
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ
- የአኗኗር ዘይቤ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በማለት ሲዘረዝሩ መምህር ሁለት ደግሞ የተማሪዎቹ የስህተት ምንጭ ሊሆን ከሚችሉት ምክንያቶች አንዱ ከ 1_4ኛ ክፍል በአማርኛ መምህራን አለመማራቸው እና ለትምህርቱ ሙሉ ፍላጎት ማጣት ናቸው። በማለት ሃሳባቸውን አክለዋል።

ጥያቄ 3. የጽህፈት ክህሎታቸውን ለማሻሻል የተማሪው መጽሃፍ ብቻ በቂ ነው ብለው ያስባሉ?

መምህር 1 ሲመልሱ የተማሪውን መጽሃፍ በትክክለኛ አተገባበር እና የአፈጻጸአም ሁኔታ ከተማሩ በቂ ነው። ሆኖም ግን አልፍ አልፎ ከመጽሃፍት ውጭ ቢታከልበት የበለጠ ሊያምር ይችላል በማለት መልሰዋል። መምህር 2 በመምህር 1 ሃሳብ በመስማማት ሌላ አስተያየት ሳይሰጡ የተማሪውን መጽሃፍ ብቻ መጠቀም አለመጠቀም ጉዳይ አይደለም ሌሎች ችግሮች ከተፈቱ ለመምህሩ ችግሮቹን ለመቅረፍ ቀላል ይሆንለታል በማለት ገልጸዋል።

ጥያቄ 4. የተማሪዎቹ የጽህፈት ክህሎት እንድሻሻል ምን ቢደረግ ይሻላል ብለው ያስባሉ?

መምህር 1

- ከ1-4ኛ ም ጭምር በአማርኛ መምህር ት/ቱ ቢሰጥ

- ከመማር ማሰተማር ውጭ ያሉ ችግሮች ቅድሚያ ቢቃለሉ ለምሳሌ የተማሪው መሰረታዊ ፍላጎት በማለት የችግሩን ስፋት እና ጥልቀት ጠቆም አድርገዋል።

መምህር 2

- በመምህር 1 ሃሳብ ተስማምተው የመማር ማስተማር ችግር የሚበልጠው ከክፍል ውጭ ያለው ነው ብለዋል ።ሆኖም ግን እኛም መምህራን ችግር የለብንም ማለት አይደለም ብለዋል ።

ጥያቄ 5. የጽህፈት ክሂል ለማስተማር ተጨማሪ መጽሃፍ ይጠቁምሉ?

መምህር 1 እና መምህር 2 በአንድነት በአዎንታ በጋራ መልሰውልኛል። አክለም ተጨማሪ መጽሃፍ የምንጠቀመው አልፎ አልፎ ነው ይላሉ። መመህር 2ም አክለው የተማሪው መጽሃፍ ተማሪውን የማይመጥንበት ሁኔታ እንዳለ ተናግረዋል።

ጥያቄ 6. ተማሪዎች ራሳቸውን በትክክል በጽህፈት ይገልጻሉ? ልምን?

መምህር 1 ሲመልሱ በጣት የሚቆጠሩት ተማሪዎች ሃሳቡን በትክክል ይገልጻል ለማለት አልደፍርም ብለዋል ። መምህር 2ም በበኩላቸው ሃሳባቸውን በትክክል ገለጹ ማለት በጽህፈት ክህሎታቸው የተሻሉ ናቸው ማለት ነው። ይህን የሚያሟሉት ትንሽ ተማሪዎች እንደሚሆኑ እርግጠኛ ነኝ ብለዋል ።የተደረገውም ቃለ ምልልስ በመመሰጋገን በአክብሮት ተለያይተናል።አጥኚውም ለትምህርት ጥራት ሲባል ለሚያደርጉት ትብብር በድጋሜ በማመስገን ተለያይቷል ።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ

በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ ማጠቃለያ ሀሳብ እና የመፍትሄ ሀሳብ እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያዥነት ያላቸው ዝርዝር ጉዳዮች በቅደም ተከተል የሚቀርቡበት ክፍል ነው።

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ሦስት መሰረታዊ ወይም መሪ ጥያቄዎችን በመመለስ ላይ ያተኮረ ነው ። ጥናቱ በጋምቤላ ክልላዊ መንግስት በማጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ በሰሙይ 1ኛ ደረጃ ትምህት ቤት በሚገኙ አፋቸውን በማጃንግ ቋንቋ የፈቱ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ያነጣጠረ ነው።

እነዚህም ተጠኝ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች መፈተሽና መተንተን ሲሆን ጥናቱም ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን የሚመልስ ይሆናል። እነሱም ፡-

• በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ድረሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንምን ናቸው?

• በማጃንግ ቋንቋ አፍ የፈቱ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጫቸው ምንድነው?

•በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ የሚገኙ ስህተቶች አይነትና መጠን እንድሁም ድግግሞሽ ምንያህል ነው? የሚሉት ናቸው።

ለነዚህም መሰረታዊ ጥያቄዎች የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም ተጠኝ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ ለተኳሪ ተማሪዎች የድርሰት ፈተና በመስጠት የጽሁፍ መጠይቅ በማቅረብ እና ምላሻቸውን በመቀበል እንድሁም የተጠኝ ተማሪዎች የአማርኛ መምህራንን ቃለመጠይቅ በማድርግ ለመሰረታዊ ጥያቄዎቹ መልስ መስጠት ተችሏል ። በዚህም መሰረት በተተኳር ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰት ውስጥ የተፈጸሙ አጠቃላይ ስህተቶች ብዛት በድርሰት አንድ ላይ ብቻ ከ2510 የቃላት ብዛት 1455 ስህተቶች የተፈጸሙ ሲሆን ይህም ስህተት 810 የሚሆኑት የሆሄያት ስህተት ነው። የሥርዓተ-ነጥብ ስህተት ደግሞ 560 ይሆናል ። የቃላት አጠቃቀም ስህተት 55 ሆኖ ተገኝቷል። መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ደግሞ 30 ሲሆን ይህም ከ50 ተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት የተገኘ ነው።

በድርሰት ሁለት ደግሞ ከ3080 ጠቅላላቃላት ብዛት የሆሄያት ግድፈት 960 የሥርዓተ-ነጥብ ስህተት 400 የቃላት አጠቃቀም ስህተት 50 እንድሁም መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች 40 ሲሆን በድምሩም 1440 ስህተቶች በተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት ተፈጽሟል ።

በሁለተኛ ደረጃ የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ የሆነው ተጠኝ ተማሪዎች በድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጫቸው ምንድንነው? የሚል ነው። በዚህ ጥናትም ከተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያዎች እንደተገኘው ወይም እነደታየው ምንጮቹ የውስጥ ቋንቋ ተጽዕኖ፣የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪዎች ፣ የመማር ማስተማር ዘዴ እና ስነ ልበናዊ ሁነታዎች እንደሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል።

በዚህ ጥናት መሰረት በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት የሚያሳየው በማጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ በሰሙይ ትምህርት ቤት የሚገኙ የማጃንግ ቋንቋ በአፍ መፍቻነት የሚገለገሉ የሰባተኛ ክፍል ተጠኝ ተማሪዎች በሁለቱም ድርሰቶች በጥናቱ የተረጋገጠው የስህተት ምንጫቸው የውስጥ ቋንቋ ተጽዕኖ ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች ፣ የማስተማሪያ መሳሪዎች ፣ ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ኑሮ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳየናል።

### 5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

አጥኝው ከተገኘው የጥናት ውጤት አንጻር ተጠኝ ተማሪዎች ለወደፊቱ ከዚህ በታች ያሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች በተግባር ላይ ቢያውሏቸው የድርሰት ጽሁፍ ላይ ለውጥ ይመጣል ብሎ ያምናል ለተግባሩም የሚመለከታቸው አካላት ወይም በትምህርት መስክ ላይ የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ የድርሻቸውን እንዲወጡ በትህተና እጠይቃለሁ። መፍትሄዎቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ከቅድመ መደበኛ እስከ አራተኛ ክፍል ላሉት ተማሪዎች በአማርኛ መምህራን ትምህርት ቢሰጥ።
- ተማሪዎች የቋንቋውን ህግና ሥረዓትን ከመማራቸው በፊት ፍደላትን ቅርጽና ድምጽ በቅድሚያ ለይተው ቢያውቁ።
- መምህራን በተማሪው መጽሀፍ ላይ የሚሰጡትን የጽሁፍ መልመጃዎች በሥረዓት ቢተገብሩ።
- በአጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የጽሁፍን ወኔ የሚቀሰቅሱ የተለያዩ የጽሁፍ ውድድሮች ቢካሄዱ ።
- ለተጠኝ ተማሪዎች እና ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የተለያዩ ግንዛቤዎችን ፈጥሮ ተማሪዎች በምግብ ማነስም ሆነ እጥረት ምክንያት ከትምህርት ቤት እንዳይቀሩ እና በሰዓቱ እንዲገኙ ቢደረግ ለትምህርት ጥራቱ የራሱን አስተዋጾ ያደርጋል።
- በትምህርት ቤቱ የሚካሄደውን የፊደላት ቅርጽና ድምጽ ልዩነት በመርጃ መሳሪያ የተደገፈ ቢሆን።

ከላይ የተጠቀሱት የመፍትሄ ሀሳቦች ወደተግባር ቢቀየሩ የተማሪዎች የጽሁፍ ብቃት ደረጃ እንደሚሻሻል አጥኝው ያምናል።

## ዋቢ ጽሁፎች

ልዕልሰገድ አሰፋ። (1987) ። *"በወላይተኛ እና ሲዳመኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማረኛ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና"* ለአርትስ ማስተር ድግሪ  የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ አድስ አበባ ዮኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

መሰረት  ጣፋ። (2003) ።*"በሃረማያ እና በአደሎ ከፍተኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማረኛ በሚጽፉበት ወቅት የሚፈጽሟቸው ዋናዋና የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና"* ለአርትስ ማስተር ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ አድስ አበባ ዮኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

ምህረት ሳዳሞ። (1998) ። *"በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተን ደረጃ ትምህርት ቤት በሃድየኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማረኛ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና"*። ለአርትስ ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ አድስ አበባ ዮንቨርስቲ (ያልታተመ) ።

ባየ ይማም። (1987) ። *የአማረኛ ሰዋሰው።* አድስ አበባ፣ ት. መ. ማ. ማ. ድ. ።

ተስፋየ ሽዋየ። (1981) *። "ስነልሳንን እና ቋንቋን ማስተማር* መግቢያ"።አድስ አበባ ዮኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

ተገኘ አህመድ። (2000) *። "አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማረኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና ።"* ለአርትስ ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ አድስ አበባ ዮኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

አለም እሸቱ። (1995)። *"በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀት እና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር።* ከጥቅምት 25_29/1995 ዓ ም ለአማረኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጀ የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርቶች ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ።" (ያልታተመ)።

አማረ ማሞ። (1986)። *የልቦለድ ድርሰት አጻጻፍ መሰረታዊ መመሪያ።* አድስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

አማረ ሰውነት። (1996)። *"በትግረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማረኛ ሲጽፉ የሚፍጽሟቸው ስነልሳናዊ ስህተቶች"*። ለአርትስ ማስተር ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ። አድስ አበባ ዮኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቀ። (2009)። *የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር*። አድስ አበባ ሊትማን መጽህፍት ማተሚያ ቤት።

ግርማ ሃይሉ። (2000)። *"በጌድዎኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማረኛ ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና"*። ለአርትስ ማስተር ድግሪ ማሙያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ፣ አድስ አበባ ዮኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

Allwright.D and K.M Bailey.(1991) *focuss on the Language classroom research for Language teachers*. Cambrdge .cambradge university press.

Atkinson.D. (2003) "*L2writing in the past process era .introduction on ".jprnal of second language writing*. 12:3_15

Badger, R and white, G.(2000) "*product ,process and gener :approch to writing in EAP*"(electronic version) ELT jornal 54(2), 153_160

Badger,R & White. G .(2000) *aprocess gener approch to teaching writing* point ELT jornal,54(2) 153_160

Baskoff .F(1972). *Language learning* Philadelphia center for curriculum development 22.1

Bayern.D. (1988). *Teaching writing skills*. Hong Kong long man group (F.E) ltd.

Brown .H.(1994). *Principles of Language learning and teaching*. New jersey. Prentice Hall regents.

Bruning , R. and Horn .C(2000) *developing motivation to write*. Educational Psycologiest. 35(1) 25_37

Burns, A.(2001) *gener_ based approch to writing and begning adult ESL learners*. Inc.candlil and Nmercer(eds) English language teaching in social context : Areader (pp 200_207) London Routledge

Casanave , C. P(2013) *controversies in second language writing*:Dilemmas and dissicions inreserch and instructons. University of Michigan press

Celce.M .(1991). *Teaching English as second Language* (ed) Boston. Heinle and Heinle publishers.

Corder .S.P .(1967) *the significance of learner error*. IRAL. Vol.1_4:161_169.

Dubin, F& E.Olshtain (1986). *Course design* : developing programs and materials for language learning Cambridge : Cambridge university press

Dulay,H.Burt. S.Krashen .(1982). *Language two*. Newyork oxford. Oxford university press

Ellis,R.(1989). *Understanding second languge acqussition*. Oxford :oxford university press

Ferris , D.(1995) "*student reaction to teachers reponse in multiple draft composition classrooms*"TESOL .quarterly.29

Fisher, R.(2012) *teaching writing* :asituted dynamic point British Educational research jornal .38(2).299_317

Gere, A.(1987) *writing groups*:history theory and implication siu press.

Grabe, W. and Kaplan ,R.B(2014) *theory and practice of writing* :An applied linguistic perspective Routledge.

Harmer, J . (1983) *the practice of English languge teaching*. London : long man press

Harmer, J .(1991) *the practice of English language teaching* London :Long man group. UK limtd.

Heaton ,J.(1975). *Writing English language tests*.London :Longman Inc.

Hedgcock , J. and Lefkowitz, N.(1994) *feedback on feedback*: assessing learner receptivity to teacher response in L2 composing jornal of second language writing.3(2) 141_163

Hedge & T. (1988). *Writing* .Hong Kong: Oxford : Oxford university press

Hyland, K.(2003) *second language writing* Hong Kong, Cambridge university press

Johns, A.(2003) *gener and Esl/EFL composition instruction*.Inexploring the dynamics of second language writing .Barbara Kroll (Eds).(pp 195_217) Combridge: Combridge university press

Keh, C. (1990) *feedback in the process* : amodel and methods for implementation

Kellogg, R. and Raulerson ,B.(2007) *Improving the writing skills of collage students.* Psyconomic Bulletin and Review.14(2).237_242

Knapp, P.and Watkins,M.(2005) *gener, text. Grammer*: technologies for teaching and assessing writing. UNSW press

Krashen, S.(1987). *Principle and practice in second language Acquisition* prentice hall international (UK) LTD.

Kroll, B. (1990) . *Second language writing*. Cambridge, Cambridge university press

Lado, R (1964) *language testing* . NewYork: MC. Graw Hill book company.

Lee, M and I.L. (1997). *Guidelines Aperiodical for classroom language teachers in SEAME*(ed) facilitating in the language classroom. Vol.19 No.2pp.73_103.oxford graphic printers ltd.

Leki (1991) *Coaching from the margins*,: issues in writing response in KROLLB.(ed) language witing:research insight for the classroom.

Littlewood , W. (1984). *Foregin and second language learning* . Cambridge : Cambridge university press

Matsuda, P.K. (2003)" *Pocess and post process* "adis cursive history jornal of second language writing (12)63_85

Negera, E.A. (1983) *"none_contrastive errors in African English* :type and significance " IRAL.vol 21 no.2 pp 35_45.

Norish , J. (1990). *language learning and their errors* ,modern English publication.

Norrish, H.J (1983) *language lerners and their reesr*"London and Basing stock: mcmillan publisher Ltd.

Nuan .D (1989). *Design tasks for the communicative classroom* . Cambridge : Cambridge university press

Pincas , A.(1982) *teaching English writing* London :Rergmam press LTD. Vol 23 No 3 pp 359_360

Pincas ,A.(1982) *teaching English writing* .London: macmilan press LTD.

Raimes, A. (1983). Techniques in teaching writing .oxford , oxford university press

Richards ,J.(1990). *The language teaching matrix*. Cambridge: Cambridge university press

Seow,A.(2002) "*the writing process and process writing*"in jack C.Ric.hadrds ,Willy , A.Renandya(Eds) methodology of curunt practice (pp 315_300) Combridge. New York Combridge university press

Silva, T.(1990) *second language composition instruction*: DevelopmentS, issus and directions. IB. Kroll (Ed) second language writing: researche in sites for the classroom.(pp11_21) Combridge: Combridge university press

Silva,T.(1990)"*second language composition instruction* :development issue and directions in Esc" second language writing in Barbara kroll (ed) Cambridge: Cambridge university press

TangerPermpoon, T.(2008) *integrated approch to improve students writing skill for English measure students*.ABAC jornal 28(2) 1_9

Trimmer , J and M.(1988). *Writing with purpose* ,Boston:Houghtonmigglin company.

Trimmer, J and James , M.(1988) *writing with purpose*. Boston :Houghton Mifflin campaney

Tsui,A. and Ng,M.(2000) *Do secondary L2 writers benefit from per comments*: jornal of secondary language writing .9(2)147_170

Ur,P.(1996) *course in language teaching practice and theory* . Cambridge: Cambridge university press

Weigle , S.C(2002) *assessing writing* 4th ed. Cambridge, UK : Cambridge university

White , R. (1980) *teaching written English* :practice language. London Jorge Allen Unwin.

Whtite , R .(1980) *Teaching writing English* London: George Allen and Un winpublisher.

Widdowson , H.(1990) *aspects of language teaching* .oxford :oxford university press

Williams , J.(2014) *prepring to teach writing* :Research theory and practice Woutledge.

Yan , G (2005) *Aprocess Gener model for teaching writing* English teaching forum.43(3) 18_26

Zamel , V. (1983). *responding to students writing*. TESL quarterly 19,79_101Boston University and Massachusetts.

## አባሪዎች

## አባሪ አንድ

### ለተማሪዎች የቀረቡት የድርሰት ርዕስ አማራጮች

ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጅማ ዮኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሁማኒቲስ

ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ

አማረኛ ትምህርት ክፍል

**1. የህይወት ታሪክ**

**2. የዛፍ ጥቅም**

**3. የባህላዊ ጨሞ አፈላል**

**4. የውኃ ጥቅም**

**5. የትምህርት ጥቅም**

**6. የሀገር ፍቅር**

**አባሪ ሁለት**

## በጥናቱ የሚገኙ ምህጻረ ቃላት

ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጅማ ዮኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሁማኒቲስ

ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ

አማረኛ ትምህርት ክፍል

**ጠቃብ ፦ ጠቅላላ ቃላት ብዛት**

**ስነአስ ፦  ስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት**

**ሆአስ ፦ ሆሂያት አጻጻፍ ስህተት**


**ስድብ ፦ ስርዝ ድልዝ ብዛት**


**ጠስብ ፦ ጠቅላላ ስህተት ብዛት**


**ቃአስ፦ ቃላት አጠቃቀም ስህተት**

**መያስ ፦ መለየት ያልተቻለ ስህተት**


## አባሪ ሶስት ድርሰት አንድ










**1.** አባሪ አራት **ድርሰት ሁለት**







## 2. አባሪ አምስት የጽሁፍ መጠይቅ



ጅማ ዩኒቨርሲቲ
ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ
የኢ/ያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ት/ት ክፍል
በተማሪዎች የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው ለሰሙይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የ7ኛ ክፍል የማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ነው። አላማውም ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሙትን ስህተት መለየትና የስህተቱን ምንጭ መጠቆም እንዲሁም መፍትሔ ማፈላለግ ነው።

"ስለትብብራችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ"

ትዕዛዝ አንድ

ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጭ/

1ኛ. ድርሰት እንድትፅፉ የአማርኛ መ/ራችሁ ያዛችኋል?

ሀ/ አንዳንድ ጊዜ ለ/ ሁል ጊዜ ሐ/ አልፎ አልፎ መ/ ተሰጥቶ አያውቅም

2ኛ. የፅሑፍ የቤት ስራ ይሰጣችኋል?


ሀ/ አንዳንድ ጊዜ ለ/ ሁል ጊዜ ሐ/ አልፎ አልፎ መ/አንድስም

3ኛ. የፃፋችሁትን የፅሁፍ የቤት ስራ መ/ራችሁ ያርማሉ?

ሀ/ ሁል ጊዜ ለ/ አንዳንድ ጊዜ ሐ/ ብዙ ጊዜ መ/ አይታረምም

4ኛ. በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ለመፃፍ ያለህ/ያለሽ ፍላጎት ምን ያህል ነው?

ሀ/ከፍተኛ ለ/ ዝቅተኛ ሐ/ መካከለኛ መ/ ምንም ፍላጎት የለኝም



5ኛ. የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ላይ ያለውን የፅሑፍ መልመጃ ትሰራላችሁ?

ሀ/ አልፎ አልፎ ለ/ ሁሉንም ሐ/ አንሰራም መ/ እርግጠኛ አይደለሁም

6ኛ. የአማርኛ መ/ራችሁ ከመማሪያ መፅሃፍት ውጭ ያስተምሯችኋል?

ሀ/ አንዳንድ ጊዜ ለ/ ብዙ ጊዜ ሐ/ አያስተምሩንም መ/ እርግጠኛ አይደለሁም

7ኛ. በአማርኛ ድርሰት መፅሐፍ ይከብድሃል/ሻል/?

ሀ/ በጣም ለ/ ብዙም አይከብደኝም ሐ/ ቀላል ነው መ/ አንዳንድ ጊዜ

ትዕዛዝ ሁለት


አጭር መልስ ስጥ/ጭ/

8ኛ. በአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ የሚያስቸግሩ ሁኔታዎች ምንምን ናቸው?

9ኛ. በአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ወይም ለማሻሻል ምን ይደረግ ትላለህ/ሽ/?

10ኛ. በአማርኛ ድርሰት ስትፅፍ የሚፈጠረው ስህተት ምክንያት ምን ይመስልሃል/ሻል/?

## 3. አባሪ ስድስት ቃለ መጠይቅ



ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢ/ያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ት/ት ክፍል

በስሙ-ጅ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የአማርኛ መ/ራን የሚመለስ ቃለ መጠይቅ

ይህ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው በስሙ-ጅ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ለሚያስተምሩ የአማርኛ መ/ራን ሲሆን አላማውም በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት በሚፅፉበት ወቅት የሚፈፅሙት ስህተት መለየት፣የስህተት ምንጫቸውን መጠቆምና መፍትሔ ማፈላለግ ነው።

"ስለትብብራችሁ በቅድሚያ እናመሰግናለሁ"

1ኛ. በማጃንግ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በፅህፈት ወቅት የሚፈፅሙት ስህተት ምንምን ናቸው?

2ኛ. የስህተት ምንጫቸው ምን ይመስልሃል ብለው ይገምታሉ?

3ኛ. የፅህፈት ክህሎታቸውን ለማሻሻል የተማሪው መፅሐፍ ብቻ በቂ ነው ብለው ያስባሉ?

4ኛ. የተማሪዎቹ የፅህፈት ክህሎት እንዲሻሻል ምን ቢደረግ ይሻላል ብለው ያስባሉ?

5ኛ. የፅህፈትን ክህል ለማስተማር ተጨማሪ መፅሐፍ ይጠቀማሉ?

6ኛ. ተማሪዎች ሃሳባቸውን በትክክል በፅህፈት ይገልፃሉ? ለምን?